# መጽሐፈ ሄኖክ



## “ወለመዋዕል አርአየኒ ዑርኤል መልአክ”

ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ

የተቀበልነው የአንድምታ ትርጓሜ


<u>አሳታሚ፡-</u>

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፳፻ወ፫ዓ.ም.



ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፤
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት
ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት ፤

የቴሌግራም ቻናላችንን ለማግኘት

@amharicbooks24

ይሄን ይጫኑ

# መ ግ ለ ጫ

"ምርሐኒ እግዚኦ ፍኖተ እንተ ባቲ አሐውር" መዝ ፻፵፪.፰

የኢትዮጳጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተክርስቲያን እንደ መሆኗ ሁሉ በዓለም ከምትታወቅባቸው ዐበይት መገለጫዎች ውስጥ በዋቢነት የሚጠቀሱት ቢጥንታውያን ብሔራዊውን ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ ተጠብቀው ከቆዩት የብሉያት አንድምታ ትርጓሜ በዓለም እስከ አሁን የሌለው ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብቻ ተጠብቆ የቆየው መጽሐፈ ሄኖክ ነው።

በብሂለ አበው "ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዐለ መጽሐፍ" እንደተባለው የያሬድ ልጅ ሄኖክ ትውልዱ ከቀደሙት አባቶች ሲሆን የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ ከቁጥር ፲፬ -፲፯ እንደጻፈው ከአዳም ጀምሮ እስከ ራሱ ማለትም እስከ ሄኖክ ድረስ ሲቆጠር ሰባት ትውልድ ይሆናል።

ይኸውም :-

፩. አዳም
፪. ሴት
፫. ሄኖስ
፬. ቃይናን
፭. መላልኤል
፮. ያሬድ
፯. ሄኖክ ናቸው።

እርሱም ባለ ዘመኑ ሁሉ በፍጹም እምነት እግዚአብሔርን እያገለገለ ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወልዶ በምድር ላይ የኖረበት እድሜው ፫፻፷፭ ዓመት መሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፳፫

ሄኖክም አካሄዱን (በጎ ሥራውን) ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር ስለወሰደው (ስለሰወረው) አልተገኘም።

እርሱም ስለ መላእክት አኗኗር፣ ስለጥፋት ውሀ ከጥፋት ውሃ በኋላ ስለሚኖረው ቀጣይ ዘመን፣ ስለ ፀሐይ፣ ስለ ጨረቃና ከዋክብት መመላለስ (ዑደት) ስለ መሲሕ (ክርስቶስ) ወደ ዓለም መምጣትና ከቅድስት ድንግል (ማርያም) መወለድ ፣ ዓለምን ስለማዳኑና ስለ ዕለተ ምጽዓት ፍርድ አሰጣጥ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ ከቁጥር ፲፬ - ፲፭ በጻፈው መሠረት ተገልጾለት ተናግሯል።

ይህ ሆኖ ሳለ እንደሌለ ሆኖ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይታወቅና የማይገኝ መጽሐፈ ሄኖክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያናችን ሊቃውንት ከጥንት ጀምሮ በጉባኤ ቤት ለደቀመዛሙርቶቻቸው ሲያስተምሩት እንደኖሩ ይታወቃል። አሁን ግን እግዚአብሔር የፈቀደው ጊዜ ደርሶ በሊቃውንት ታይቶና ተመርምሮ በማሳተሚያ ድርጅታችን አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለትምህርትም ሆነ ለታሪክ እንዲጠበቅ ማድረጋችንን ስንገልጽ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

"ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ"

አባ ጳውሎስ (ዶክተር) ቀዳማዊ ፣ ፓትርያርክ
ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስትያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና የዓለም
ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት!



የቅኔና የመጻሕፍተ ብሉያት መምህር የነበሩት

መጋቤ ምስጢር ጌራወርቅ ጥበቡ

# መቅድም

ዘሄኖክ ፡ ነቢይ ፤
ሄኖክ ፡ ማለት ፡ ተሐድሶ ፡ ማለት ነው ፤ አዳም ፡ በምግብ ፡ ምክንያት ፡ ብልየትን ፡ እንዳመጣ ፤ ሄኖክም ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ ተሐድሶን አምጥቷልና ፤ አንድም ፡ ዛሬ ፡ በብሉይ ፡ ሥጋ ፡ ገነት ፡ እንደ ገባ ፡ እኛም ፡ ኋላ ፡ ተነሥተን ፡ በሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንገባለንና ፡ በሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ ተነሥተን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለመግባታችንም ፡ ምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በጎረ ፡ ገነት በምግባር ፣ በሃይማኖት ፣ ጸንቶ ፡ ኖረ ፤ መላእክት ፡ ፍጥረታትን ሁሉ ፡ አሳይተውት ፡ ፀሐይን ፡ ጨረቃን ፣ ከዋክብትንም ፣ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጽፏል ፣ ይህንም ፡ ሄኖክን ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ ለመዝለፍ ፡ አስነሥቶታል ። እሊህ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከሴት ፡ ርቀን ፣ ንጽሕ ፡ ጠብቀን ፡ እንኖራለን ፤ ብለው ፡ ተሳሉ ፤ ደቂቀ ፡ ቃየል ፡ የወገብ ፡ ድባ ፡ እያደረጉ ፡ ራቁታቸውን ፡ ሁነው ፡ ሲንጠላጠሉ ፡ አይተው ፡ ሂደው ፣ ተጋብተዋል ፤ አንድም ፡ ለጉዳያቸው ፡ ከወጡ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አለሌ ፣ እንደ ፡ ባዝራ ፡ ይንጠላጠሉ ፡ ጀመሩ ፤ ይህን ፡ አይተው ፡ በሐፀ ፡ ዝሙት ፡ ተነደፉ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተሰነካከለዋል ፤ መነኰሴ ፡ ለመፍቅደ ፡ ደብር ፡ ወጥቶ ፡ በግብረ ፡ ዓለም ፡ ተሰቦ ፡ እንዲቀር ፤ በአያቱ ፡ በቤተ ፡ መላልኤል ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፤ ሁለት ፡ ራእይ ፡ አይቷል ፤ ሰማይ ፡ ይትሀየድ ፡ ወይትነጻሕ ፡ ብሎ ፡ የማየ ፡ አይኅን ፡ ነገር ፡ ተናግሯል ፤ ወጽአ ፡ ላሕም ፡ ፀዐዳ ፡ ብሎ ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚደረገውን ፡ ተናግሯል ፤ ይህንም ፡ ሄኖክን ፡ ዘውእቱ ፡ ሳብዕ ፡ እም አዳም ፡ ይለዋል ፣ አዳም ፣ ሴት ፣ ሄኖስ ፣ ቃይናን ፣ መላልኤል ፣ ያሬድ ፣ ሄኖክ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ተጽፎ ፡ ሲነበብ ፡ ሲተረጐም ፡ ከነቢያት ፡ እስከ ፡ ሐዋርያት ፡ ደረሰ ፤ ሐዋርያት ፡ መጻሕፍትን ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ ሲሰጡ ፣ ሄኖክን ፡ በልባቸው ፡ ቈጥረው ፡ በአፋቸው ፡ ሳይቈጥሩት ፡ ቀርተዋል ፤ ስለምን ፡ ቢሉ ፣ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ጽርዓውያን ፡ አምነዋል ፤ ሄኖክ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጾለት

ሦስተኛው አኪቢኤል ፤
ጣሚኤል ፤
አራተኛው ፡ ጣሚኤል ፤
ራሙኤል ፤
አምስተኛው ፡ ራሙኤል ፤
ዳንኤል ፤
ስድስተኛው ፡ ዳንኤል ፤
ኤዜቃኤል ፤
ሰባተኛው ፡ ኤዜቃኤል ፤
ሱሩቃያል ፤
ስምንተኛው ፡ ሱሩቃያል ፤
አስኤል ፤
ዘጠነኛው ፡ አስኤል ፤
አርሞርስ ፤
አሥረኛው ፡ አርሞርስ ፤
በጥርኤል ፤
አሥራ ፡ አንደኛው ፡ በጥርኤል
አናንኤል ፤
አሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ አናንኤል
ዘቂቢ ፤
አሥራ፡ ሦስተኛው፡ ዘቂቢ ፤
ሳምሳፒኤል፤
አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ሳምሳ
ፒኤል፤
ሰርትኤል ፤
አሥራ፡አምስተኛው፡ሰርትኤል ፤
ጡርኤል ፤
አሥራ፡ስድስተኛው፡ጡርኤል ፤
ዮምያኤል ፤
አሥራ፡ሰባተኛው፡ዮምያኤል ፤
አራዝያል ፤
አሥራ፡ስምንተኛው፡አራዝያል፡
ነው ፤

እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሐበይቶሙ፡ለ፪ቱ፡
፻ት ፡ መላእክት ፤
የሁለቱ፡መቶ፡አለቆች፡እሊህ ፡
ናቸው ፤
ወባዕዳንሂ ፡ ኵሉ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ሌሎችም ፤ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፤
ከዚህ፡ አሥራ፡ ስምንት ፡ ቈጠረ ፤
ሦስቱን ፡ ኋላ ፡ ያመጣቸዋል ፤
አንድም፡ እሉ ፡ እሙንቱ፡ ፪ቱ፡
፻ት ፡ መላእክት ፡ ሐበይቶሙ ፤
አለቆች፡እሊህ፡ናቸው ፤ ሁለት፡
መቶ ፡ ናቸው ፡ ወባዕዳን ፤ በየጊ
ዜው ፡ የሚነሱ ፡ ናቸው ፤
፱ ፤ ወነሥኡ ፡ ሎሙ ፡ አንስትያ ፡
ከእነርሱም ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፤
ወኀረየ ፡ ኵሉ ፡ ለለርእሱ አሐተ ፡
አሐተ ፤
ሁሉም ፡ ለየራሱ አንዳንዲቱን
መረጠ ፤
፲ ፤ ወወጠኑ ፡ ይባኡ ፡ ኀቤሆን ፡
ወተደመሩ ፡ ምስሌሆን ፤
ወደነእርሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡
ጀመሩ ፤ ከእነርሱም፡ጋራ፡አንድ፡
ሆኑ ፤ በግብር ፡ አወቁአቸው ፤
፲፩ ፤ ወመሀርዎን ፡ ሥራያተ ፤
ሥር ፡ መማስን ፡ ቅጠል ፡ መበ
ጠስን ፤
ወስብዐታተ ፤
ጋኔን ፡ መሳብን ፡ አስተማሩአ
ቸው ፤
ወመቲረ ፡ ሥርው ፤

ወራእየ ፡ገጹ፡ ለክቡር፡ወስቡሕ፤
የከበረ ፡ የተመሰገነ ፡ ፊቱንም ፡
ማየት ፡ አይችልም፤
ወኢይክል ፡ መኑሂ ፡ ዘሥጋ ፡
ይርአይ ፡ ኪያሁ ፡ እሳተ ፤
ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ ሰው ፡ እሱን፡
ያይ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ አይቻለ
ውም፤
፳፩ ፤ እሳት ፡ ዘይነድድ ፡ በዓውዱ፤
በዙሪያው ፡የሚነድ ፡እሳት፡ አለ፤
መላእክት ፡ ናቸው ፤
ወእሳት ፡ ዓቢይ ፡ይቀውም ፡ ቅድሜሁ ፤
በፊቱ ፡ ከንፈ ፡ ሰቀላውን ፡ የያዘ ፡
የእሳት ፡ ዓምድ ፡ አለ፤ አንድም ፡
ደጀ ፡ጠኚ ፡ መልአክ ፡ በፊቱ ፡
አለ ፤
፳፪ ፤ ወአልቦ ፡ ዘይቀርብ ፡ ኀቤሁ ፡
እምእለ ፡ ዐውዱ ፡ ትእልፊተ ፡ ትዕል
ፊት ፡ ቅድሜሁ ፤
በዙሪያው ፡ ካሉ ፡ መላእክትም
ወደ ፡ እርሱ ፡ የሚቀርብ ፡ የለም፡
የብዙ ፡ ብዙ ፡ መላእክትም ፡
በፊቱ ፡ አሉ ፤
፳፫ ፤ ወውእቱሰ ፡ ኢይፈቅድ ፡
ምክረ ፡ ቅድስተ ፤
ጽንዕተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እርሱ ፡
ግን ፡ ጽኑ ፡ ምክር ፡ አይሻም ፤
አምላክነቱ ፣ ፈጣሪነቱ ፣ ጌትነቱ ፡
ያራራዋልና ፤ እስመ፡ቅንየትከ ፡
ወምልክናከ ፡ ይሬስየከ ፡ ትሠሃል፡
ሳዕለ ፡ ኵሉ[፩] ፡ እንዲል፤ አንድም፡
ከባሕርዩ ፡ የተለየ ፡ ምክር ፡
አይወድም ፡ አለ ፤ ሰው ፡ ሊመክ
ረው ፡ አይሻም ፤
፳፬ ፤ ወቅዱሳን ፡ እለ ፡ ይቀርቡ ፡
ኀቤሁ ፡ ኢይርኅቁ፡ መዓልተ ወሌሊተ ፤
ወእልቦ፡ ዘይቀርብ ፡ ብሎ ፡ አልነ
በረምን ፡ቢሉ ኢይርኅቁ፡ ማለቱ ፡
ባለሟልነታቸውን ፡ ሲያይ ፣ ወአ
ልቦ ፡ ዘይቀርብ ፡ ማለቱ ፡ ባሕ
ርዩን፡መርምሮ ፡የሚያውቀው ፡
የለም፡ ሲል ፡ ነው ፤
ወኢይትአተቱ ፡ እምኔሁ ፣
ከእርሱ፡ ፊጽመው ፡አይርቁም ፤
፳፭ ፤ ወአነ ፡ ሀሎኩ ፡ እስከ ፡ ዝንቱ ፡
ዲበ ፡ ገጽየ ፡ ግልባቤ ፡ እንዘ ፡ እር
ዕድ ፤
እንዲህ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ እየተ
ንቀጠቀጥሁ ፡ ፊቴን ፡ ተከናንቤ
ነበር ፤
፳፮ ፤ ወእግዚእ ፡ በአፉሁ ፡ ጸውዐኒ ፡
ወይቤለኒ ፡ ቅረብ ፡ ዝየ ፡ ሄኖክ ፡
ወለቃልየ ፡ ቅዱስ ፤
ስምያ ፡ ተአዘዞ ፡ ያለበት ፡ ነው፤
ጌታም ፡ በአንደበቱ ፡ ጠርቶ ፡
ሄኖክ ፡ ወደዚህ ፡ቅረብ ፤ቃሌን፡
ስማ ፤ አንድም ለቃሌ ፡ ታዘዝ፡
አለኝ ፤
፳፯ ፤ ወአንሥአኒ ፡ ወአቅረበኒ ፡ ኀበ፡
ኆኅት ፤
አንሥቶም ፡ እስከ ፡ ደጃፉ ፡ ድረስ ፡
አቀረበኝ፡ ወደቁ ፡ ብሎ ነበርና፡
አስነሳኝ ፤
ወአንሰ ፡ ገጽየ ፡ ታሕተ ፡ እኔጽር ፣

፩ ፣ ጥበብ ፲፪፥፲፮

ዋው ፡ ሁነው ፡ ያሳየዋልና ። ለከ
ዋክብተ ፡ ሰማይ ፡ ወለኃይለ ፡
ሰማያት ። ለሰማይ ፡ ጭፍራ ፡
ከዋክብት ፡ ለነበሩ ፡ ለደቂቀ ፡
ሴት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ ሆናቸው ።
ወከዋክብት ፡ እለ ፡ ያንኰረኵሩ ፡
ዲበ ፡ እሳት ።
በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ለሚገለባበጡ
ኮከቦችም ፡ ይህ ፡ የግዞት ፡ ቤት
ሆናቸው ።
፲፭ ። ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡
ኀለፉ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምቅ
ድመ ፡ ጽባሖሙ ።
እነርሱም ፡ በእውቀት ፡ በደግነት ፡
ፍጹም ፡ ከመሆናቸው ፡ አስቀድሞ ።
እስመ ፡ ኢመጽኡ ፡ በጊዜሆሙ ።
በጊዜያቸው ፡ ጊዜ ፡ አልመጡምና ።
አንድም ፡ በጊዜያቸው ፡ ጊዜ ፡ አል
መጡምና ፡ ምንም ፡ ባይመጡ ፡
ተምዖሙ ፡ ብለህ ፡ ወደታች ፡
እሥር ።
፲፮ ። ወተምዖሙ ፡ ወአሠሮሙ ፡
እስከ ፡ ጊዜ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ኃጢአቶሙ ።
በኃጢአታቸው ፡ የመጣባቸው ፡
ፍዳ ፡ እስኪፈጸምባቸው ፡ ድረስ
ተቆጥቶ ፡ አጋዛቸው ።
በዓመተ ፡ ምሥጢር ።
ዓቢይ ፡ ዓለም ፡ መንግሥተ ፡
ሰማይ ። ለጻድቃን ፡ ዓቢይ ፡ ዓለም ።
ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ለኃጥአን ፡ የሚሰ
ጥበት ፡ ነውና ፡ ምሥጢር ፡ አለው ።
፲፯ ። ወይቤለኒ ፡ ዑርኤል ፡ በዝየ ፡
ተደሚሮሙ ፡ መላእክት ፡ ምስለ ፡
አንስት ።

ዑራኤልም ፡ በዚህ ፡ በቦታው ።
አንድም ፡ በግብሩ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡
ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁነው ።
ይቀውሙ ፡ መናፍስቲሆሙ ።
ነፍሶቻቸው ፡ በገሃነም ፡ ይኖራሉ ፡
አለ ።
፲፰ ። ወብዙኀ ፡ አርአያ ፡ ከዊኖሙ ፡
አርኰስዎሙ ፡ ለሰብእ ።
በብዙ ፡ ወገን ፡ አብነት ፡ ሁነው
ሰዎችን ፡ አረከሷቸው ። አንድም
አርኰስዎሙ ፡ ብዙኀ ፡ አርአያ ፡
ብዙኀ ፡ ብሎ ፡ ይገጥሟል ። አብነት ፡
ሁነው ፡ ፈጽመው ፡ አረከሷቸው ።
ወያስሕትዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡
ይሡዑ ፡ ለአጋንንት ፡ ከመ ፡ አማልክት ።
ምዕመናን ፡ ለሥላሴ ፡ እንዲሠዉ ፡
እነሱም ፡ ለጣዖታት ፡ ሠዉ ።
እስመ ፡ በዕለት ፡ ዓባይ ፡ ኵነኔ ፡ በዘይ
ትኴነኑ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸሙ ፡ በዕለት ፡
ዓባይ ።
ታላቅ ፡ በሆነች ፡ ቀን ፡ እስኪያጠ
ፉአቸው ፡ ድረስ ፡ ጽኑ ፡ ፍርድ ፡
በሚፈረድባት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡
በሚፈረድባቸው ፡ ገንዘብ ፡ ይፈረ
ድባቸዋልና ፡ ይሠዋሉ ።
፲፱ ። ወአንስትያሆሙኒ ፡ እስሒ
ቶን ፡ መላእክተ ፡ ሰማይ ፡ ከመ ፡ ሰላ
ማውያት ፡ ይከውና ።
ሴቶቻቸውም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ማዕ
ረግ ፡ የነበሩ ፡ የሴትን ፡ ልጆች ፡
አስተው ፡ እንደ ፡ ደኅና ፡ ይሆ
ናሉ ። ሴት ፡ መነኮሲት ፡ ወን
ዱን ፡ መነኮሴ ፡ አስታ ፡ ደኅነኛ ፡
እንድትመስል ።

## ጉባኤ

፫ ፧ ወአነ ፡ ሄኖክ ፡ ርኢኩ ፡ አር
ዐያ ፡ ባሕቲትየ ፧
እኔ ፡ ሄኖክ ፡ የብቻዬን ፡ ነገር
የብቻዬን ፡ ምሥጢር ፡ አየሁ፧
አንድም ፡ ሳይናበብ ፡ ብቻዬን ፡
ምሥጢር ፡ አየሁ ፧
አጽናፈ ፡ ኵሉ ፧
በጽንፈ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
አየሁ ፧
ወአልቦ ፡ ዘርእየ እምሰብእ ዘከመ ፡
አነ ፡ ርኢኩ ፡
እኔ ፡ እንዳየሁት ፡ ያየ ፡ የለም
አለ ፧ ራእዩ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ነውና፧
አንድም ፡ እርሱ ፡ ያየውንም ፡
ያየ ፡ የለምና ።

## ምዕራፍ ፳

፩ ፧ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አስማቲ
ሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይተግሁ ፡ ቅዱሳን ፡
መላእክት፧
ለቅዳሴ ፧ ለተልዕኮ ፧ ለተራድኦ
የሚተጉ ፧ የቅዱሳን ፡ መላእክት ፡
ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፧
፪ ፧ ዑራኤል ፡ ፩ዱ ፡ እመላእክት
ቅዱሳን ፧
ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡
ዑራኤል ፡ ነው ፧ ዑራኤል ፡ ማለት ፡
ብርሃን ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡
ነው ፧
እስመ ፡ ዘረዓም ፡ ወዘረዓድ ፧
በመብረቅ ፡ በነጐድጓድ ፡ የተሾመ ፡
ነውና ፧

፫ ፧ ሩፋኤል ፡ ፩ዱ ፡ እመላእክት ፡
ቅዱሳን ፡ ዘመናፍስተ ፡ ሰብእ ፧
ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡
ሩፋኤል ፡ ነው ፧ ሩፋኤል ፡ ማለት ፡
ፈውሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡
ነው ፧ ዘመናፍስተ ፡ ሰብእ ፡ አለው ፡
በሰው ፡ ነፍሳት ፡ ወይም ፡ በሰው ፡
ቍስል ፡ የተሾመ ፧
፬ ፧ ራጉኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት፡
ቅዱሳን ፧
ከከበሩ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡
ራጉኤል ፡ ነው ፧ ራጉኤል ፡ ማለት ፡
ራእየ ፡ እግዚአብሔር ማለት ፡
ነው ፧
ዘይትቤቀሎ ፡ ለዓለም ፧
ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚያሳልፍ ፧
ወለብርሃናት ፧
ፀሐይን ፡ ጨረቃን ፡ የሚያሳልፍ፧
ፍጡራንንስ ፡ በፍጡር ፡ እጅ ፡ አያ
ሳልፋቸውም ፡ ብሎ ፡ ዲያብሎስን ፡
የሚበቀል ፧
ወለብርሃናት ፧
አጋንንትን ፡ የሚበቀል ፧ እስመ
ለሊሁ ፡ ሰይጣን ፡ ይትሜሰል ፡
ከመ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ እንዲል[፩] ፧
አንድም ፡ ህየንተ ፡ ብርሃናት ፡ ቢል ፡
ስለ ፡ ጻድቃን ፡ ዲያብሎስን ፡ የሚ
በቀል ፧
፭ ፧ ሚካኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡
ቅዱሳን ፧
ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡
ሚካኤል ፡ ነው ፧ ሚካኤል ፡ ማለት፡
መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ማለት ፡
ነው ፧ ዕፁብ ፡ ነገርም ፡ ይለዋል ፧

፩ ፤ ፪ኛ ቆሮ. ፲፩ ፡ ፲፬

ስድስተኛ ፡ ያየው ፡ደብረ ፡ ታቦር ፡ ነው ፣ በዚያ ፡ ያሉ ፡ ባርቅ ፡ ዲቦራ ፡ ናቸው ፤ ሰባተኛ ፡ ያየው ፡ ቀራንዮ ፡ ነው ፣ በዚያ ፡ ያሉ ፡ ጌታ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ፣ ሳብዕ ፡ ያለው ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ነው ፣ አሁን ፡ ለተራራው ፡ እንዲህ ፡ያለ ፣ ማእከል ፡ አለው ፤ በምሥራቅ ፡ ያሉ ፡ ገነት ፣ ደብር ፡ ቅዱስ ፣ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ ናቸው ፤ በምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፤ ደብረ ፡ ታቦር ፣ ቀራንዮ ፣ ናቸው ፣ መካከሉ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ነው ፣

፯ ፤ ወየዐውድዎ ፡ ዕፀወ ፡ መዓዛ ፣ መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ እንጨቶች ፡ ከበውታል ፣ ማለት ፡ ሕገጋቱ ፡ ከበውታል ፣

ወሀሎ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ዕፅ ፡ አልቦ ፡ ግሙራ ፡ አመ ፡ ፄነወኒ ፡ ወኢአሐዱ እምውስቴቶሙ ፤

በመካከላቸውም ፡ አንድ ፡ እንጨት ፡ አለ ፣ በሸተተኝም ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሳቸው ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ የሸተተኝ ፡ የለም ፤ አንድም ፡ ኢታምልክ ፡ በመካከላቸው ፡ አለ ፣ ከሕግጋቱም ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በመስጠት ፡ ኢታምልክን ፡የሚመስለው ፡ የለም ።

፰ ፤ ወባዕዳንሂ ፡ ዘከማሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘይምዕዝ እምኵሉ ፡ መዓዛ ፤

ኢኮነም ፡ ካለ ፡ ባዕድሂ ፣ ባዕዳንሂም ፡ ካለ ፡ ኢኮኑ ፡ ባለ ፡ በቀና ፡ ነበር ፤ በሸተተኝ ፡ ጊዜ መዓዛ ፡ ካላቸው ፡ ዕፀው ፡ እንደ እርሱ ፡የሚሸት ፡የለም ፣ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ካላቸው ፡ሕገጋት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማስጠት ፡ እንደ ፡ ኢታምልክ ፡ ያለ ፡ የለም ፤

፱ ፤ ወቈጽሉሂ ፡ ወጽጌሁ ፣ ወዕፁ ፡ ኢይጸመሂ ፡ ለዓለም ፣

ቅጠሉ ፣ አበባው ፣ እንጨቱ ፣ ለዘለዓለም ፡ አይጠወልግም ፣ ማለት ፡ በኢታምልክ ፡ የሚገኘው፡ ጸጋ ፣ ክብር ፣ አይጠፋም ፣ ማለት፡ ነው ፤

፲ ፤ ወፍሬሁኒ ፡ ሠናይ ፣

ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤

ወፍሬሁሰ ፡ ከመ ፡ አስካለ ፡ በቀልት ፤

ፍሬውም ፡ እንደ ፡ዘንባባ ፡ ፍሬ ፡ ንብብር ፡ ነው ፣ ማለት፡ በኢታምልክ ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ በፊት ፡ ለማየት፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ ማለት፡ ኢታምልክ ፡ በዓይነ ፡ ልቡና ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡የሚያሰኝ ፡ ነው ፤

፲፩ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ዕቤ ፡ ነዋ ፡ ዝንቱ ፡ ሠናይ ፡ ዕፅ ፡ ወሠናይ ፡ ለርእይ ፡ ወአዳም ፡ ቈጽሉ ፡ ወፍሬሁኒ ፡ ሞገስ ፡ ጥቀ ፡ ለርእየ ፡ ገጽ ፤

ያን ፡ ጊዜም ፡ ይህ እንጨት ፡ እነሆ ያማረ ፡ ነው ፤ ቅጠሉ ፡ ጽፍቅ ፡ ነው ፣ ፍሬው ፡ ንብብር ፡ ሊያዩትም ፡ ፈጽሞ ፡ የተወደደ ነው ፡ አልሁ ፤

፲፪ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አውሥአኒ ፤ ሚካኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡

በዘመናቸው ፡ መከራና ፡ ኃዘን ፤ መቅሠፍትና ፡ ድካምም አያገኛ ቸውም፤ (አይዳስሳቸውም) ።
፳፱ ። ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ባረክዎ ፡ ለእግዚአ ፡ ስብሐት ፡ ንጉሥ ፡ ዘለ ዓለም ።
እንደዚህም ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ ፡ ሰጥ ቷቸዋልና ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ የሚሆን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡ አመሰገንሁት አለ ።
እስመ ፡ አስተዳለወ ፡ ከመዝ ለሰብእ ጻድቃን ወከመዝ ፡ ፈጠረ ።
እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ወዳጆቹ ፡ ስለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ኢታምልክን ፡ አዘጋጅቷልና ።
ወይቤ ፡ የሀብምሙ ።
ይህን ፡ ዕፅ ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ አሏልና ፤ ማለት ፡ በኢታምልክ ፡ የሚገኘውን ፡ ሥርዓት ፡ ያስተም ሯቸው ፡ ዘንድ ፡ አስተምሯቸው ፡ ብሎ ፡ አሏልና ፡ አመሰገንሁት ። አንድም ፡ ሳብዕ ፡ ደብር ፡ ቀራን ዮን ፡ ማዕከል ፡ አለው ። በም ሥራቅ ፡ ያሉ ፡ ገነት ፤ ደብር፡ ቅዱስ ፤ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፤ ደብረ ፡ ዘይት ፤ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ናቸው ። መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ ዕፀው ፡ ከበውታል ፡ ማለት ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታት፡ መከራ ፡ ከበውታል ፤ መከራ፡ የሚቀበሉ ፡ ጌታን ፡ አብነት ፡ እያደረጉ ፡ ነውና ። በውስጣቸው፡ ከእርሳቸው ፡ መዓዛ ፡ የሚበልጥ፡ ዕፅ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማሰጠት ፡ ከሰማዕታት ፡ የሚበ ልጥ ፡የጌታ ፡ መስቀል ፡ አለ። በሽተተ ፡ ጊዜ ፡ በመዓዛ ፡ የሚመ ስለው ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማስጠት ፡ የሚመስ ለው ፡ የለም ። ጻድቃን ፡ ሰማዕ ታት ፡ እንከበርበት ፡ ብለው ፡ ነው ። እሱ ፡ ግን፡ እከብር ፡ አይል ፡ ክቡር ። እጸድቅ ፡ አይል ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ። ቅጠሉ ፤ አበ ባው ፤ እንጨቱ ፡ አይጠወልግም ፤ ማለት ፡ በመስቀል ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ አይጠፋም ፤ ፍሬው ፡ ንብ ብር ፡ ነው ። ማለት ፡ በመስቀል ፡ የሚገኘው ፡ ክብር፡ ብዙ ፡ ነው ። ለፊት ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ማለት ፡ መስቀል ፡ ለዓይነ ፡ ሕሊና ፡ ደስ ፡ ያሰኛል፤ ያንጊዜ ፡ ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ የዚህን ፡ ዕፅን ፡ ነገር ፡ ልታውቅ፡ ትወዳለህ ? ማለት ፡ የጌታን ፡ መከራ ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ? አለኝ ፤ ማወቅስ ፡ ሁሉንም ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ፤ ይልቁንም፡ የዚህን ፡ ዕፅ፡ ነገር ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ። ማለት ፡ ማወቅስ ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታ ትን ፡ መከራ ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ፤ ይልቁንም ፡ የጌታን ፡ መስቀል ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ። ራሱ ፡ የጌታን ፡ ዙፋን ፡ የሚመስለው ፡

ረጅም ፡ ሁኖ ፡ ያየኸው ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ሊጉበኛት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀመጥበት ፡ የእግዚአብሔር ዙፋን ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ለማዳን ፡ ሥጋውን ፡ ቈርሶ ፣ ደሙን ፡ አፍስሶ ፡ ባዳ ነው ፡ ጊዜ ፡ የሚሰቀልበት ፡ መስቀል ፡ ነው ፤ ከሥጋዊ ፡ ከደ ማዊ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ይነካው ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፤ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር የሚያሰጥ ፡ መስቀልን ፡ ማጥፋት ፡ የሚቻለው ፡ የለም፤ አይሁድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፤ ሮማውያን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፤ የቀበሩት ፡ መስቀል ፡ ተነሥቶባቸዋልና ፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ዕንጨት ፡ ፍሬ ፡ ይሰጣል ፤ ማለት ፡ በምግባር ፡ በሃ ይማኖት ፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ በመስቀል ፡ ከሚገኘው ፡ ክብር ፡ ይሰጣል ፡ ማለት ፡ ነው፤ በመ ስዕ ፡ በኩል ፡ ይተከላል ፡ ማለት ፡ ወደመስዕ ፡ ፊቱን ፡ መልሰው ፡ ጌታን ፡ ሰቅለውታልና ፡ በመካን ፡ ቅዱስ ፡ ማለት ፡ በቀራንዮ ፤ መንገለ ፡ ቤቱ ፡ ማለት ፡ ቀራ ንዮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አጠ ገብ ፡ ነውና ፤ ከዚህ ፡ ዕፅ ፡ በበሉ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ማለት ፡ ይህን ፡ የመስቀልን ፡ ፀጋ ፡ ክብር ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡ ደስ ይላቸዋል ፤

ዕፀው ፡ ሁሉ ፡ በየወገናቸው ፡ መዓዛ ፡ ያገቡለታል ፡ ማለት ፤ ምዕመናን ፡ ለመስቀል ፡ ምስጋና ፡ ያገቡለታል ፤ መስቀል ፡ ኃይልነ ፤ መስቀል ፡ ጽንዕነ ፣ የማይለው ፡ የለምና ፤ ከዚህ ፡ ዕፅ ፡ የበሉ ፡ ሰዎች ፡ በሕይወት እንዲኖሩ ፣ እንግዲህም ፡ የሚነሱ ፡ ሰዎች ከዚህ ፡ ዕፅ ፡ እየበሉ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፤ ማለት ፡ በመስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ ያድነናል ብለው ፡ አምነው ፡ በሕይወት ፡ እንደኖሩ ፡ ዛሬም ፡ በመስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ አድኖናል ፡ ብለው ፡ አምነው ፡ በሕይወት ፡ይኖራሉ፤ በዘመናቸው ፡ ይህን ፡ በበሉበት ወራት ፡ ኀዘን ፡ ድካም ፣ የለም ፣ ማለት ፤ መስቀልን ፡ ባመኑበት፡ ወራት ፡ ኀዘነ ፡ ሥጋ ፣ ኃዘነ ፡ ነፍስ ፣ ድካመ ፡ ሥጋ ፡ ድካመ፡ ነፍስ ፡ የለባቸውም ፤ ይህን ፡ ዕፅ ፡ አዘጋጅቶላቸዋልና ፤ ይህን ዕፅ ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ አዝዟልና፣ማለት ፤ መስቀልን ፡ አዘጋጅቶላቸዋልና ፣ በመስቀል፡ የሚገኘውን ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ጻድቃን ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አዘጋጅቷልና ፡ አመሰገንሁት ፤ አንድም ፡ ስድስቱ ተራሮች ፡ ማለት ፡ በስድስቱ ፡ ቃላተ ፡ ወንጌል ፡ ያመኑ ፡ ናቸው፤ ሳብዕ፡ ደብር ፡ እመቤታችን ፣ ዕፀው ፡

ሁሉ ፡ ከበውታል ፤ ማለት ፡ የጻድቃን ፡ ንጽሕና ፡ ቅድስና ፡ ድንግልና ፡ ከበውታል ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በውስጣቸው ፡ ያለውን፡ አንዱን ፡ የሚመስለው ፡ የለም፤ ማለት ፡ የእመቤታችንን ፡ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ ከጻድቃን ፡ ንጽሕና ፡ ድንግልና ፡ የሚመስለው ፡ የለም ፤ ቅጠሉ ፡ አበባው ፡ አይጠወልግም ፡ ማለት ፡ በእመቤታችን ፡ ድንግልና ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ አይጠፋም ፤ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ዘምባባ ፡ ንብብር ነው ፤ ማለት ፡ በእመቤታችን ፡ ድንግልና ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ለዓይን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በእመቤታችን ፡ ድንግልና ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ለዓይነ ፡ ልቡና ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ ያንጊዜ ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ የዚህን ፡ የዕፅ ፡ ነገር ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ? አለኝ ፡ ማለት ፡ የእመቤታችንን ፡ ንጽሕናዋን ፡ ድንግልናዋን ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ? አለኝ ፤ ማወቅስ ፡ መላውን ፡ ዕፅ ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፡ ይልቁንም ፡ የዚህን ፡ ዕፅ ፡ ነገር ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፤ ማለት ፡ ማወቅስ ፡ የጻድቃንንም ፡ ንጽሕና ፤ ድንግልና ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፤ ይልቁንም ፡ የእመቤታችንን ፡ ድንግልና ፤ ንጽሕና ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፡ አልሁት ፤ ራሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዙፋን ፡ የሚመስል ፡ ረጅም ፡ ሁኖ ፡ የምታየው ፡ ዓለምን ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ይጐበኘው ፤ ዘንድ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ዙፋኑ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚያድርባት ፡ እመቤታችን ፡ ናት ፤ ከሥጋዊ ፤ ከደማዊ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ይህን ፡ ዕፅ ፡ ይነካው ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፤ ማለት ፡ የእመቤታችንን ፡ ንጽሕና ፤ ድንግልና ፡ የሚያጠፋው የለም ፤ አይሁድ ፡ እሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ ብለውታል ፤ አንጢዲቁማርያጦስ ፡ ያፑስያውያን ፡ ሲያውያን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፀረ ፡ ማርያም ፡ ይላቸዋል ፤ ባንድ ፡ ስም ፡ ሲሆን ፡ አንጢዲቁማርያጦስ ፡ ዘውእቱ ፡ ፀረ ፡ ማርያም ፡ እምድኅረ ወለደቶ ፡ ለእግዚእነ ፡ ተደመረት ምስለ ፡ ዮሴፍ ፡ ብሏል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ማጥፋት ፡ አልተቻላቸውም ፡ ይለዋል ፤ የዚህ ፡ ዕፅ ፡ ፍሬ ፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣል፡ ማለት ፡ በእመቤታችን ፡ ድንግልና ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣል ፡ ማለት ፡ ነው ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን ፡ ያጣሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ መላእክት ፡ ጌታ ፡ እንዲገቡ ፡ አይተዋቸውም ፤

፲ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ተስእልክዎ ፡ ለመልአክ ፡ ሰላም ፡ ዘየሐውር፡ ምስሌየ ፡ ዘውእቱ ፡ አርአየኒ ፡ ኵሎ ፡ ዘኅቡእ ፤

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ያለው ፡ መልአኩን፡ ጠየቅሁት የተሰወረውንም ፡ ሁሉ ፡ የገለጠልኝ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤

፲፩ ፤ ወእብሎ ፡ መኑ ፡ ውእቶሙ ፡ እሉ ፡ አርባዕቱ ፡ ገጽ ፡ ዘርኢኩ ፡ ወእለ ፡ሰማዕኩ ፡ ቃሎሙ፡ ወጸሐፍክዎሙ ፤

ያየኋቸው ፤ ቃላቸውንም ፡ የሰማሁት ፡ እሊህ ፡ አራቱ ፡ መላእክትን ፡ ቈጠርኋቸው ፤ እነ ፡ ማናቸው ? ብዬ ፡ ፋኑኤልን ፡ ጠየቅሁት፤ ፋኑኤል ፡ ማለት ፡ ማኀፈደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤

፲፪ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዝ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ መሐሪ ፡ ወርኁቀ ፡ መዓት ፡ ቅዱስ ሚካኤል ፤

እርሱም ፡ መጀመሪያው ፡ ቃል፡ ይቅር ፡ የሚል ፡ ከመዓትም ፡ የራቀ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡ አለኝ፤

፲፫ ፤ ወካልዕ ፡ ዘዲበ ፡ ኵሉ፡ ሕማም ፤

ሁለተኛውም ፡ በበሽታው ፡ ሁሉ ላይ ፤

ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ ቍስል ፡ ዘውሉደ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ሩፋኤል ፤

በሰው ፡ ልጆችም ፡ ቍስል ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ቅዱስ ሩፋኤል ፡ ነው ፡ አለኝ ፤

፲፬ ፤ ወሣልስ ፡ ዘዲበ ፡ ኵሉ ፡ ኃይል ፡ ውእቱ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፤

ሦስተኛውም ፡ በመላእክት ፡ ሁሉ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡ አለኝ ፤

፲፭ ፤ ወራብዕ ፡ ዘዲበ ፡ ንስሓ ፡ ለተስፋ ፡ እለ ፡ ይወርሱ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ውእቱ ፡ ፋኑኤል ፤

አራተኛውም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ለሚወርሱ ፡ ሰዎች ፡ ተስፋ ፡ ሊሆን ፡ ንስሐ ፡ በሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ፋኑኤል ፡ ነው ፡ አለኝ፤

፲፮ ፤ ወእሉ ፡ ፬ቱ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል፤

ከፍ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አራቱ ፡ መልእክተኞች ፡ እሊህ ናቸው ፤ አንድም ፡ አሁን ፡ አስቀድሞ ፡ የተናገራቸው ፤ አንድም፡ አራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ናቸው ፤

ወ፬ተ ፡ ቃለ ፡ ሰማዕኩ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፤

በዚያም ፡ ወራት ፡ አራቱን ፡ ቃሎች ፡ ሰማሁ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፲፩

፩ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ርኢኩ ፡ ኵሎ፡ ኅቡኣቲሆሙ ፡ ለሰማያት ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡ የተሰወሩ ፡ ምሥጢሮችን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ፡
፪ ፡ ወመንግሥት ፡ እፎ ፡ ትትከፈል ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተመጥኖ ፡ ተመጥኖ ፡ እንዲሰጥ ፡ አየሁ ፡
ወተግባረ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ በመዳልው ፡ ይዴለው፡
የሰው ፡ ምግባሩ ፡ ትሩፋቱ ፡ እንዲመዘን ፡ የትሩፋቱ ፡ዋጋ ፡ ተመጥኖ ፡ እንዲሰጥ ፡ አየሁ፡
፫ ፡ ወበህየ ፡ ርኢኩ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ለኅሩያን ፡ ወማኅደሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የተመረጡ ፡ የጻድቃን፡ ማደሪያ ፡ መንግሥተ፡ ሰማይን ፡ አየሁ ፡
፬ ፡ ወርእያ ፡ አዕይንትየ ፡ በህየ ፡ ኵሎሙ ኃጥአን ፡ እንዘ ፡ ይሰደዱ ፡ እምህየ ፡ እለ ፡ ይክህድዎ ፡ ለስመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡
የመላእክት ፡ ጌታን ፡ ስም ፡ የካዱ ፡ ኃጥአንም ፡ ሁሉ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ወጥተው ፡ ሲሰደዱ ፡ ዓይኖቼ ፡ አዩ ፡
፭ ፡ ወይስሕብዎሙ ፡
መላእክት ፡ ስበው ፡ ያወጧቸዋል ፡
ወቀዊም ፡ አልቦሙ ፡ በመቅሠፍት ፡ እንተ ፡ ትወፅእ ፡ እምእግዚአ ፡ መናፍስት ፡
ከመላእክት ፡ ጌታ ፡ በምትወጣ ፡ መቅሰፍት ፡ በመከራው ፡ መጽናት፡ አይቻላቸውም፡
፮ ፡ ወበህየ ፡ ርእያ ፡ አዕይንትየ ፡ ኅቡኣተ ፡ መባርቅት ፡ ወነጕድጓድ ፡
ከዚያም ፡ቦታ ፡ የነጕድጓድ ፡ የመባርቅት ፡ ምሥጢርን ፡ አየሁ ፡
ወኅቡኣተ ፡ ነፋሳት፡
የነፋሳትንም ፡ ቦታ ፡ አየሁ ፡
ወእፎ ፡ ይትከፈሉ ፡ ከመ ፡ ይንፍሑ ዲበ ፡ ምድር፡
በዚህም ፡ዓለም ፡ ነፋሳት ፡ ተመጥነው ፡ ተመጥነው ፡ እንዲወጡ ፡ አየሁ ፡
ኅቡኣተ ፡ ደመና ፡ ወጠል ፡
የጠልና ፡ የደመናትን ፡ ምሥጢር ፡ አየሁ ፡
፯ ፡ ወበህየ ፡ ርኢኩ ፡ እምኀበ፡ ይወፅኡ ፡ በውእቱ ፡ መካን ፡
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የሚወጡበትን ፡ አየሁ ፡
ወእምህየ ፡ ይጸግቡ ፡ ጸበለ ፡ ምድር፡
ይጸግቡም ፡ ካለ ፡ ፀበላት ፡ ጸበልም ፡ ካለ ፡ ይፀግብ ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበር ፡ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ ከደመናውም ፡ የምድር ፡ ትቢያዎች ፡ ዝናሙን ይጠግባሉ፡

የሰው ፡ ተሥዕሎተ ፡ መልክዐ ፡ አንድ ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ከኪሩቤል እንደ ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ አለ ፤ እንደ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡ አለ ፤ ገብርኤል ፡ ማለት ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ማለት ፡ ነውና ፤

፳፩ ፤ ወተስእልክዎ ፡ ለአሐዱ ፡ እመላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘየሐውር ፡ ምስሌየ ፡ ወዅሎ ፡ ኅቡአተ ፡ ዘአርአየኒ ፡ በእንተ ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፤

ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ የተሰወረውንም ፡ ሁሉ ፡ የገለጠልኝ ፡ ከከበሩ ፡ መላእክት ፡ አንዱን ፡ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ የዚህን ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ጠየቅሁት ፤

፳፪ ፤ ወእቤሎ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ወእምአይቴ ፡ ይከውን ፡ ውእቱ ፡ ወበእንተ ፡ ምንት ፡ ምስለ ፡ ርእሰ ፡ መዋዕል ፡ የሐውር ፤

ይህ ፡ ማነው ? ከወዴትስ ፡ ተገኘ ? ከብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ስለምን ፡ ተቀመጠ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ፡

፳፫ ፤ ወአውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ ዘሎቱ ፡ ኮነ ፡ ጽድቅ ፤

ትንቢት ፡ የተነገረለት ፡ ከሰው ፡ የተወለደው ፡ ክርስቶስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።

ወጽድቅ ፡ ምስሌሁ ፡ ኃደረ ፤

ትንቢት ፡ የተፈጸመለት ፤ አንድም ፡ ትንቢት ፡ የተነገረለት ፡ የተፈጸመለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።

አንድም ፡ ወጽድቅ ፡ ምስሌሁ ፤ የባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፤

ወዅሎ ፡ መዛግብተ ፡ ዘኅቡዕ ፡ ውእቱ ፡ ይከሥት ፡ እስመ ፡ እግዚአ መናፍስት ፡ ኪያሁ ፡ ኀረየ ፤

አብ ፡ ክርስቶስን ፡ መርጧልና ፤ ክርስቶስ ፡ የተወሐደው ፡ ሥጋን መርጧልና ፤ እርሱ ፡ የተሠወረውን ፡ ምሥጢር ፡ ይገልጣል ፤

፳፬ ፤ ወዘክፍሉ ፡ ኵሉ ፡ ሞአ ፤

ዕድሉ ፡ ሥጋ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፤

በርትዕ ፡ ለዓለም ፤

ለዘለዓለም ፡ በሚገባ ፡ ነው ፤ ተዋሕዶ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ወዘዅሎ ፡ ሞዐ ፡ ይላል ፤ ኃጣውእን ፡ አጋንትን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ በለበሰው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤

፳፭ ፤ ወዝንቱ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ዘርኢከ ፡ ያነሥኦሙ ፡ ለነገሥት ወለኃያላን ፡ እምስካባቲሆሙ ፡ ወለጽኑዓን ፡ እመናብርቲሆሙ ፤

ይህ ፡ ያየኸው ፡ ወልደ ፡ አዳም ኃያላኑን ፡ ከሹመታቸው ፡ ይሽራቸዋል ፤ ጽኑዓኑንም ፡ ከዙፋናቸው ፡ ያወርዳቸዋል ፤

## ምዕራፍ ፲፰

፩ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ነስሐ ፡ ርእሰ ፡ መዋዕል ፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ጌታ ፡ አዘነ ፤ ሰው ፡ አሁን ፡ ሲያውቅ ፡ ሥራውን ፡ ሠርቶ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ እንዲጸጸት ፤ ተጸጸተ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ ለበጎ ፡ አብነት ፡ አድርጌ ፡ ብፈጥራቸው ፡ ለክፉ ፡ አብነት ፡ ሆኑ ፡ ብሎ ፡ ተጸጸተ ፤
ወይቤ ፡ በከ ፡ አኅጕልክዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ የብስ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ኃጢአታቸው አጠፋኋቸው ፤ አንድም ፡ ብላሽ ሁነው ፡ ሊቀሩ ፡ አጠፋኋቸው ፤
፪ ፤ ወመሐለ ፡ በስሙ ፡ ዓቢይ ፡ ከመ ፡ እምይእዜ ፡ ኢይገብር ፡ ከመዝ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ዲበ ፡ የብስ ፤
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እንዳላደርግ ፡ ሕያውየ ብሎ ፡ ማለ ፤
፫ ፤ ወትእምርተ ፡ እወዲ ፡ በሰማይ ፡ ወይከውን ፡ ማዕከሌየ ፤
ቀስተ ፡ ደመናውን ፡ ምልክት ፡ አድርጌ ፡ በሰማይ ፡ አሳያለሁ ፤
ወማእከሌሆሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ መጠነ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ዲበ ፡ ምድር ፤
በእኔና ፡ በእርሳቸው ፡ መካከል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሰማይን ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ መተማመኛ ፡ ይሆናል ፤
፬ ፤ ወእምዝ ፡ በትእዛዝየ ፡ ውእቱ ፡ ሶበ ፡ ፈቀድኩ ፡ ከመ ፡ አጽንዮሙ ፡ በእደ ፡ መላእክት ፤
አጽንቼ ፡ በትእዛዜ ፡ ልጣላቸው ብወድ ፡ በእደ ፡ መላእክት ፡ ነው ፤ አንድም ፡ በእደ ፡ መላእክትም አጽንቼ ፡ ነው ፤ ልጣላቸው ፡ ብወድ ፡ በትእዛዜ ፡ ነው ፤
፭ ፤ በዕለተ ፡ ምንዳቤ ፡ ወሕማም ፡ ፍጹም ፡ መከራ ፡ በሚቀበሉበት ቀን ፡ በእደ ፡ መላእክት ፡ ነው ፤
እምቅድመዝ ፡ መዓትየ ፡ ወመቅሠፍትየ ፡ የኀድር ፡ ላዕሌሆሙ ፤
ተቈጥቼ ፡ በእደ ፡ መላእክት ፡ ከማመጣው ፡ መቅሠፍት ፡ አስቀድሞ ፡ በቃል ፡ አመጣለሁ ፤ መዓቴ ፡ መቅሠፍቴ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ታድርባቸዋለች ፤ አንድም ፡ እምቅድመዝ ፡ ባለው ፡ ቁሞ ፡ ከመዓቴ ፤ ከመቅሠፍቴ ፡ አስቀድሞ ፡ መዓቴ ፤ መቅሠፍቴ ፡ ታድርባቸዋለች ፤ አንድም ፡ መልቶ ፡ ይጽፏል ፤ እምቅድመዝ ፡ መዓትየ ፡ ወመቅሠፍትየ ፡ ተኀድር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መዓትየ ፡ ወመቅሠ

ፋርስ ፡ ትውጣቸዋለች ፤ አን ድም ፡ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፤ እለ ፡ ብልጣሶር፡ኃጢአት ፡ በሚ ሠሩበት ፣ ጣዖት ፡ በሚያመል ኩበት ፡ ወራት ፡ ይሰበሰባሉ ፤ አንድም ፡ ወይወድዩ ፤ የፋርስ፡ የሚዶንን ሰዎች ፡ ለማምጣት ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሳሉ ፤ የሐውስዎሙ ፤ ነገሥታቱን ፡ ኑ ፡ ማርኩን ፡ ብለው፡ ያነዋውጧቸዋል ፤ ኃጢ አት ፡ መሥራት ፣ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ማርኩን ፡ ማለት ፡ ነውና ፤ መንፈስ ፡ ሀውክ ፤ በእለብልጣሶር ፡ ልቡና ፡ ኃጢ አት ፡ ሥሩ ፡ የሚል ፡ ሁከት ፡ ያለበት ፡ ልቡና፡ያድርባቸዋል ፤

ወየሀውክዎሙ ፤

ነገሥታቱን ፡ ማርኩን ፡ ብለው፡ ያውኳቸዋል ፤ ኃጢአት ፡ መሥ ራት ፣ ጣዖት ፡ ማምለክ ፣ ማር ኩን ፡ ማለት ፡ ነውና ፤ አንድም፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ በሚጠፉ በት ፡ እስራኤልን ፡ በበደሉበት፡ ወራት ፡ እለቂሮስ ፡ እለ፡ ዳር ዮስ ፡ ይሰባሰባሉ ፤ ወይወድዩ ፣ የፋርስን ፡ የሜዶንን ፡ ጦር ፡ ለመ ሰብሰብ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሳሉ ፤ ወየሐው ስዎሙ ፤ ያነዋውጧቸዋል ፤ ያለ ፡ ፈቃዳቸው ፡ እርዱን ፡ ብለው ፤ አንድም ፡ እለ ፡ ብልጣሶር ፡ ያነ ዋውጧቸዋል ፡ በሞት፣ መንፈስ፡ ሀውክ ፤ ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል፡ የሑከት፡ ልቡና ፡ ያድርባቸዋል፤ ወየሀውክዎሙ ፤ ያለ ፡ ልባቸው ፡ እርዱን ፡ ብለው ፡ ያውኳቸዋል ፤ አንድም ፡ እለብልጦሶርን ፡ በሞት ፡ ያነዋውጧቸዋል ፤ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ወከመ ፡ አዝእብት ፣ እለ ፡ ቂሮስ ፡ እለ ፡ ዳርዮስ ፡ እንደ ፡ ተራብ ፡ ጅብ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ በማስፈራት ፡ ይመጣሉ ፤ ወየዐርጉ ፣ ወደፋርስ ፡ ይዘምታሉ ፣ ወይከይድዋ ፡ ለም ድር ፣ እሳቸውን ፡ የመረጡ ፡ የባቢሎን ፡ ምድር ፤ አንድም ፡ እሳቸው ፡ የመረጧቸው ፡ የባቢ ሎንን ፡ ምድር ፤ አንድም ፡ ኅሩያን ፡ ዚአሁ ፡ ቢል ፣ ጌታ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ መርጧቸው ፡ የነበሩ ፡ የባቢሎንን ፡ ምድር ፡ እለቂሮስ ፡ እለዳርዮስ ፡ ይረግጧ ታል ፤ ምክያደ ፣ የእነቂሮስ ፡ የእነዳርዮስ ፡ መገሳገሻ ፡ ትሆና ለች ፤ ወሀገረ ፡ ጻድቃን፡ዚአየ ፣ የትሩፋን ፡ ሀገር ፡ ለፈረሶቻቸው ፡ መሰናክል ፡ ትሆናለች ፤ ወያን ሥኡ ፡ ቀትለ ፣ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እርስ በርሳቸው ፡ ይዋ ጋሉ ፤ አንድም ፡ የባቢሎንና ፡ የፋርስ ፡ ሰዎች ፡ ይዋጋሉ ፤ ሌላውን ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ይወጉ ፡ ነበረና ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አለ ፤ ወትጸንዕ ፣ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ያንዱ ፡ ሥልጣን ፡

፴፰ ፤ እሉንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ርኢኩ ፡ እስከ ፡ ገነተ ፡ ጻድቃን ፤

ጻድቃን ፡ እስካሉበት ፡ ገነት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ትች ፡ ነው ፤ እን ዲህ ፡ እንዲህ ፡ አየሁ ፤ ብሔሞ ትና ፡ ሌዋታን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተፈጥረው ፡ አንዱ ፡ በየብስ ፣ አንዱ ፡ ከባሕሩ ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በዋሻ ፡ ሲኖሩ ፡ ምን ፡ ተመግበው ፡ ይኖ ራሉ ? ብዬ ፡ ጠየቅሁት ፤

፴፱ ፤ ወይቤለኒ ፡ መልአክ ፡ ሰላም ፡ ዘምስሌየ ፡ ይሄሉ ፤

ይቤለኒና ፡ ይቤለኒ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከእኔ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ያለው ፡ ባልደረባዬ ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

እሉ ፡ ክልኤቱ ፡ አናብርት ፡ ላዕለ ፡ ዕበይ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ድልዋን ፡ ይሴሰዩ ፡ በከመ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በከ ፤

እኒህ ፡ ሁለቱ ፡ አውሬዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍቱ ፡ ረሀብ ፡ በክ ፡ (ከንቱ) ፡ ልታ ደርጋቸው ፡ እንዳትመጣ ፡ ይመ ገቡ ፡ ዘንድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ፤ አንድም ፡ ድልዋን ፡ ቢል ፡ የተ ዘጋጁ ፡ ሁነው ፤ አንድም ፡ ድልዋን ፡ ቢል ፡ ተዘጋጅተው ፡ ይመገባሉ ፡

፵ ፤ ወይትቀተሉ ፡ ደቂቅ ፡ ምስለ ፡ እማቲሆሙ ፤

እምተቀትሉ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከናቶቻቸው ፡ ጋራ ፤

ወውሉድ ፡ ምስለ ፡ አበዊሆሙ ፤

ወንዶች ፡ ልጆችም ፡ ከአባቶቻ ቸው ፡ ጋራ ፡ እሊህን ፡ ቢያዩ ፡ በሞቱ ፡ ነበር ፤

ሶበ ፡ ተዐርፍ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ዲቤሆሙ ፡ ተዐርፍ ፤

የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡ በምትመጣበት ፡ ጊዜ ፡ በእለ ፡ ብሔ ሞት ፡ ታርፋለች ፡ ታሳልፋቸዋ ለች ፤

፵፩ ፤ ከመ ፡ ኢትምጻእ ፡ መቅሠፍቱ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ በከ ፤

ከምጽአት ፡ አስቀድሞ ፡ ዛሬ ፡ መቅሠፍቱ ፡ በክ(ከንቱ) ፡ ልታደር ጋቸው ፡ እንዳትመጣ ፤

ዲበ ፡ እሉ ፡ ድኅረ ፡ ትከውን ፡ ኵነኔ በምሕረቱ ፡ ወበትዕግሥቱ ፤

በቸርነቱ ፣ በትዕግሥቱ ፣ ኋላ ፡ ትሆናለች ፤ ኋላ ፡ ያሳልፋቸዋል ፤ በድለው ፡ ይታገሣቸዋል ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ በቸርነቱ ፡ አኑሮ ፡ ያሳ ልፋቸዋል ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ድልዋን ፡ ይሴሰዩ ፡ ይመገቡ ፡ ዘንድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ፤ አንድም ፡ ድልዋነ ፡ ቢል ፡ የተዘጋጁ ፡ ሁነው ፡ ይመገባሉ ፤ በከመ ፡ መቅሠፍቱ ፤ እነርሱን ፡ የመገበ ፡ ይመግበ ናል ፡ በማይሉ ፡ ሰዎች ፡ እነርሱን ፡

ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
እንተሰ ፡ በአማን ፡ ጥበብ ፡ ቀዳ
ሚሃ ፡ ንጽሕት ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሜ ፡
በኵር ፡ ቃለ ፡ አብ [፩] ፡ እንዲል ፣
አካላዊ ፡ ቃልን ፡ ያመሰግኑታል ፤
አንድም ፡ እንዳለው ፡ ከዝርዋን ፡
ቃላት ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ አካ
ላዊ ፡ ቃልን ፡ ያመሰግኑታል ፤
አትሪኮን ፣ አተርጋዎን ፣ ቦርፎ
ሪኮን ፣ የሚባሉ ፡ አሉና ፤ አን
ድም ፡ ከፀሐይ ፡ አስቀድሞ ፡
የነበረ ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ ያመሰ
ግኑታል ፤
ወይሴብሕዎ ፡ በጥበብ ፤
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተቃኙ ፤
፲፪ ፤ ወይጠበቡ ፡ በነገር ፤
በነገር ፡ እየተራቀቁ ፣ ባንድነቱ ፡
ምንታዌ ፤ በሦስትነቱ ፡ ርባዔ ፡
ሳይጨምሩ ፤
ወበመንፈሰ ፡ ሕይወት ፤
ሕይወት ፡ በሚሆን ፡ በመንፈስ
ቅዱስ ፡ እየተቃኙ ፡ ያመሰግናሉ ፤
ወእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡
ስብሐቲሁ ፡ አንበሮ ፡ ለኅሩይ ፤
የማሕፀኑን ፡ መልሶ ፡ መናገር ፡
ነው ፤ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡
ክርስቶስን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡
አስቀመጠው ፤
፲፫ ፤ ወይኄንን ፡ ኵሉ ፡ ግብሮሙ ፡
ለቅዱሳን ፡ በመልዕልተ ፡ ሰማያት ፤

፩ ፤ ያዕቆብ ፡ ፫ ፥ ፲፯

ጻድቃን ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡
አውቆ ፡ በሰማይ ፡ ይፈርዳል ፤
ወበመዳልው ፡ ይደለው ፡ ምግባሮሙ
ለኵሎሙ ፤
ሥራቸው ፡ በፍትሐ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ይመረመራል ፤
፲፬ ፤ ወሶበ ፡ ያሌዕል ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡
ይኰንን ፡ ፍናቶሙ ፡ እንተ ፡ ኅብዐት
በነገረ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፤
በስሙ ፡ እምነው ፡ ሰውረው ፡
የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አውቆ ፡ ይፈ
ርድ ፡ ዘንድ ፡ አንገቱን ፡ ባቀና ፡
ጊዜ ፤
ወአሠረ ፡ ዚአሆሙ ፡ በፍኖተ ፡ ኵነኔ
ጽድቅ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፤
በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በእው
ነተኛ ፡ ሕጉ ፡ ፀንተው ፡ የሠሩ
ትን ፡ አውቆ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡
አንገቱን ፡ ባቀና ፡ ጊዜ ፤
፲፭ ፤ ይትናገሩ ፡ ኵሉሙ ፡ በ፩ዱ ፡
ቃል ፤
ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ያመሰ
ግናሉ ፤
ወይባርኩ ፡ ወይሴብሑ ፡ ወያሌዕሉ ፡
ወይዌድሱ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚአ ፡
መናፍስት ፤
ፈጽመው ፡ ያመሰግናሉ ፤ የመላ
እክት ፡ ጌታ ፡ ስምንም ፡ ያከብ
ራሉ ፤ ያመሰግናሉ ፤
፲፮ ፤ ወይጼውዕ ፡ ኵሉ ፡ ኃይለ ፡
ሰማያት ፡ ወኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡
ዘመልዕልት ፤

ወለኃያላን ፣ ወለእለ ፡ የኀድርዋ ፡
ለምድር ፤
ገዥ ፡የሚሆን ፡ ጌታም ፡ በዚህ፡
ዓለም ፡ ለሚኖሩት ፡ ለኃያላን ፣
ለጽኑዓን ፣ ለልዑላን ፣ ነገሥታት ፡
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡
አዘዘ ፤

፳፮ ፤ ወይብል ፡ ክሥቱ ፡ አዕይንቲ
ክሙ ፤
ዓይነ ፡ ልቦናችሁን ፡ ግለጡ ፤
ወአንሥኡ ፡ አቅርንቲክሙ ፤
ሥልጣናችሁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
አድርጉ ፤
እመ ፡ ትክሉ ፡ አእምሮቶ ፡ ለኅሩይ፤
ኅሩይ ፡ ክርስቶስን ፡ ማወቅ ፡
ይቻላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ አለ ፤

፳፯ ፤ ወነበረ ፡ እግዚእ ፡ መናፍስት ፡
ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፤
እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ክርስቶስ
በዙፋኑ ፡ (በጌትነት) ፡ተቀመጠ፤
ወመንፈሰ፡ ጽድቅ ፡ ተክዕወ፡ ዲቤሁ፣
የባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ
ቅዱስ ፡ በእርሱ ፡ ተገለጸ ፤ የማ
ሕፀኑን ፡ መልሶ ፡ መናገር ፡
ነው ፤

፳፰ ፤ ወነገረ ፡ አፉሁ ፡ ይቀትል ፡
ኵሎ ፡ ኃጥአነ ፤
ሐሩ ፡ እምኔየ ፡ ያለው ፡ ቃሉ
ኃጥአንን ፡ ያጠፋል ፤
ወኵሉ ፡ ዓማፅያነ ፡ ወእምገጹ ፡
ይትኀጐሉ ፤
በደለኞችንም ፡ ሁሉ ፡ ይገድላል ፤
ማለት፡ ሐሩ ፡ እምኔየ፡ይላል ፣
እነርሱም ፡ ከፊቱ ፡ ይጠፋሉ ፤

፳፱ ፤ ወይቀውሙ ፡ በይእቲ፡ ዕለት ፡
ኵሎሙ ፡ ነገሥት ፡ ወአዚዛን ፣ ወልዑ
ላን ፣ ወእለ ፡ ይእኀዝዋ ፡ ለምድር ፤
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ነገሥታቱ ፣
ሁሉ ፡ የከበሩ ፡ ሰዎችና ፡ የጸኑ
ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ይህችንም ፡
ዓለም ፡ የሚገዙዋት ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ይቆማሉ ፤

፴ ፤ ወይሬእይዎ ፡ ወየአምርዎ ፡
ከመ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብ
ሐቲሁ ፤
በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡
ያዩታል ፤ ያውቁታል ፤
ወጻድቃን ፡ በጽድቅ ፡ ቅድሜሁ ፡
ይትኴነኑ ፤
ጻድቃን ፡ በፊቱ ፡ ይፈረድላቸ
ዋል ፤

፴፩ ፤ ወነገረ ፡ በከ ፡ አልቦ ፡ ዘይት
በሀል ፡ በቅድሜሁ ፤
በፊቱ ፡ ዋዛ ፡ ዘበሬታ ፡ ነገር ፡
የሚናገር ፡ የለም ፤

፴፪ ፤ ወይመጽእ ፡ ዲቤሆሙ ፡
ሕማም ፡ ከመ ፡ ብእሲት ፡ እንተ
ውስተ ፡ ማሕምም ፤
በምጥ ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ ሴት
በኃጥአን ፡ ላይ ፡ ጭንቅ ፣ መከራ ፡
ይመጣባቸዋል ፤
ወየዐጽባ ፡ ወሊድ ፡ ሶበ ፡ ይመጽእ ፡
ወልዳ ፡ በአፈ ፡ ማሕፀና ፤
ልጇ ፡ ከማሕፀኗ ፡ ሊወጣ ፡ በመጣ፡
ጊዜ ፡ ምጡ፡ ጭንቅ ፡ እንዲሆንባት፤

ኢያድኅነነ ፤
ይህ ፡ ሥልጣናችን ፡ አያድነንም ፡ ይላሉ ፤ ገጸ ፡ ፍትሑን ፡ አያገኙም ፤

፳፪ ፤ ወኢንረክብ ፡ ዕረፍተ ፡ ንእመን ፤
እናምን ፡ ዘንድ ፡ ዕረፍትን ፡ እናገኝም ፡ ይላሉ ፤ ገጸ ፡ ፍትሑን ፡ እያገኙም ፤
እስመ ፡ መሐይምን ፡ ውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ፡ ወበኵሉ ፡ ኵነኔሁ ፡ ወጽድቁ ፤
ጌታችን ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ በቸርነቱና ፡ በፍርዱ ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ነውና ፤

፳፫ ፤ ወገጸ ፡ ኵነኔሁ ፡ ኢይነሥእ ፤
ገጸ ፡ ፍትሑን ፡ አያገኙም ፤
ወነኀልፍ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ በእንተ ፡ ምግባሪነ ፤
በሠራነው ፡ ኃጢአታችን ፡ ተፈርዶብን ፡ ከፊቱ ፡ እንሄዳለን ፤
ወኵሉ ፡ ኃጢአትነ ፡ በጽድቅ ፤ ተኈለቈ ፡
ኃጢአታችንም ፡ ሁሉ ፡ በእውነት ፡ ተቈጠረ ፤

፳፬ ፤ ወይእዜኒ ፡ ይብልዎሙ ፡ ትጽገብ ፡ ነፍስነ ፡ እምንዋየ ፡ ዓመፃ ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ ሳለባቸው ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስርቀን ፡ ቀምተን ፡ ካጠራቀምነው ፡ ከብት ፡ ሰውነታችን ፡ ትጥገብ ፡ ይላሉ ፤ ትጸግብ ፡ ቢል ፡ ትጠግባለች ፡ ይላሉ ፤
ወኢትከልዕ ፡ ወሪዶተነ ፡ እምላህባ ፡ ለክበደ ፡ ሲኦል ፤
እምክቡድ ፡ ሲኦል ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ይህ ፡ አለመብላታችን ፡ አለመጠጣታችን ፡ ጭንቅ ፡ ወደሆነች ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ከመውረድ ፡ አትከለክለንምና ፡ ዛሬ ፡ ሰውነታችን ፡ ትጥገብ ፡ ይላሉ ፤

፳፭ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ይመልዕ ፡ ገጸሙ ፡ ጽልመተ ፤
ሑሩ ፡ ካላቸው ፡ በኋላ ፡ ፊታቸው ፡ ጨለማን ፡ ይመላል ፤
ወኃፍረተ ፡ በቅድመ ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፤
በወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ፡ በአዳም ፡ ልጅ ፡ ኃፍረትን ፤ ይሞላሉ ፤

፳፮ ፤ ወእምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ይሰደዱ ፤
ከፊቱም ፡ ተሰድደው ፡ ይሄዳሉ ፤
ወሰይፍ ፡ የኀድር ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ማዕከሎሙ ፤
በኃጥአንና ፡ በጻድቃን ፡ መካከል ሰይፍ ፡ ይመዘዛል ፡ አለ ፤ ጻድቃንንና ፡ ኃጥአንን ፡ የሚለይ ፡ ሥልጣን ፡ በፊቱ ፡ ይገለጻል ፤

፳፯ ፤ ወከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሥርዓቶሙ ፤
ለጻድቃን ፡ የሚፈርድላቸው ፤
ወኵነኔሆሙ ፡ ለእዚዛን ፤

ስምዒ፡ ቃለ ፡እግዚአብሔር፡ወተ
ወከፈ ፡ ስእለተኪ[፩] ፡ እንዲል ፤
፬ ፤ ወይቤሉ ፡ ንግረኒ ፡ ምንት ፡
ውእቱ ፡ ዘይትገበር ፡ በዲበ ፡ ምድር፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚሠራው ፡ ምን ፡
እንደሆነ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፤
፭ ፤ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ሰርሐት ፡
ምድር ፤
ምድር ፡ በደቂቀ ፡ ሴት ፡ ኃጢ
አት ፡ ደክማለችና ፤
ወአንቀልቀለት ፤
በኃጢአታቸው ፡ ተነዋውጣለችና፤
ዮጊ ፡ አነ ፡ እትኀጐል ፡ ምስሌሃ ፤
ወይስ ፡ እኔ ፡ ከእርሷ ፡ ጋራ ፡
እጠፋ ፡ እሆን ? ወይስ ፡ ይህ ፡
ጥፋቱ፡ ይቀር ፡ ይሆን ፡ አለው ፤
፮ ፤ ወበድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ኮነ
ሐውክ ፡ ዓቢይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡
ወተሰምዐ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፤
ይህን ፡ ከተናገርኩ ፡ በኋላ ፡ ሁከት ፡
ሆነ ፡ መላእክት ፡ ኄኖክን ፡ ይዘው ፡
ሲመጡ ፡ በገነት ፡ ንውጽውጽታ፡
ሆነ ፤
፯ ፤ ወወደቁ ፡ በገጽየ ፤
በግምባሬ ፡ ፍግም ፡ ብዬ ፡
ወደቅሁ ፤
ወመጽአ ፡ ሄኖክ ፡ እምሔውየ ፡
ወቆመ ፡ ኀቤየ ፡ ወይቤለኒ ፡ ለምንት
ጸራሕከ ፡ ኀቤየ ፡ ጽራሐ ፡ መሪረ ፡
ወብካየ ፤

አያቴ ፡ ሄኖክም ፡ ወደእኔ ፡
መጥቶ ፡ በአጠገቤ ፡ ቆመ ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሚያሳዝን ፡
ጽኑ ፡ ልቅሶ ፡ ለምን ፡ አለቀስህ ?
አለኝ ፤
፰ ፤ ወትእዛዝ ፡ ወጽአ ፡ እምኀበ፡
ገጹ ፡ ለእግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ዲበ ፡
እለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ የብስ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ ከመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጥ
ቷል ፤ ይህ ፡ መከራ ፡ ይቀራል ፡
መስሎህ ? ወይስ ፡ አንድነት ፡
እጠፋ ፡ መስሎህ ፤
ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይኩን ፡ ኀልቀቶሙ ፤
ጥፋታቸው ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፤
፱ ፤ እስመ ፡ አእመሩ ፡ ኵሉ ፡
ኅቡዓተ ፡ መላእክት ፤
ደቂቀ ፡ ሴት ፡ የሚያውቁትን ፡
ምሥጢረ ፡ ኃጣውእን ፡ ሁሉ ፡
አውቀዋልና ፤
ወኵሉ ፡ ግፍዐ ፡ ሰይጣናት ፡
አጋንንት ፡ የሚያውቁትን ፡ ሁሉ ፡
አውቀዋልና ፤
ወኵሉ ፡ ኃይሎሙ ፡ ኅቡዐ ፡ ለእለ ፡
ይገብሩ ፡ ሥራያተ ፤
ሥር ፡ የሚምሱ ፡ ቅጠል ፡ የሚበ
ጥሱን ፡ ሰዎች ፡ ምሥጢር ፡
አውቀዋልና ፡
ወኃይሎሙ ፡ ለኀብራት ፤
የቀለማትን ፡ ግብር ፡ አውቀዋ
ልና ፡ በሕና ፡ መንከር ፤ በእንሶስላ፡
ማቅላት ፤ በድንጋይ ፡ ማጥቈር፤

፩፤ ኢሳ. ፩፥፪

እሊህ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከተፈረ
ደባቸው ፡ በኋላ ፣ የእኒህ ፡
ውሃዎች ፡ ማቃጠል ፡ በዚያ ፡
ወራት ፡ ይለወጣልና ።

፴፱ ፤ ወሶበ ፡ የዐርጉ ፡ መላእክት ፡
ይትዌለጥ ፡ ዝኩ ፡ ማይ ፡ ዘአንቅዕት ።

መላእክት ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡
አጥፍተው ፡ ባረጉ ፡ ጊዜ ፡ ይህ
ውሃ ፡ ይለወጣል ።

ወይቈርር ።

ዋዕዩ ፡ ይቀዘቅዛል ።

፵ ፤ ወሰማዕክዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
እንዘ ፡ ያወሥእ ፡ ወይብል ።

ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ሲናገር ፣
እንዲህ ፡ ሲል ፡ ሰማሁት ።

ዛቲ ፡ ኰነኔ ፡ እንተ ፡ ይትኴነኑ ፡
መላእክት ፣ ሰማዕት ፡ ይእቲ ፡ ለነገ
ሥት ፡ ወለአዚዛን ፡ ወለእለ ፡ ይእኀ
ዝዋ ፡ ለየብስ ።

ደቂቀ ፡ ሴት ፡ የሚቀበሏት ፡ ይህች ፡
መቻያ ፡ ለነገሥታቱ ፣ ለኃያላኑ ፡
ይህችን ፡ ዓለም ፡ ለሚገዟት ፣
ጽኑዓን ፡ ሁሉ ፡ የኃጢአታቸው ፡
ምስክር ፡ ናት ።

እስመ ፡ እሉ ፡ ማያተ ፡ ኰነኔ ፡
ለፈውስ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለመላእክት ፡
ወለሞተ ፡ ሥጋሆሙ ።

እሊህ ፡ የመቻያ ፡ ውሀዎች ፡
ማየ ፡ አይኅ ፡ ይመጣብናል ፡
ብለው ፡ በአምልኮት ፡ ጸንተው ፣
ምግባር ፣ ትሩፋት ፡ ለሚሠሩ
ለመድኃኒተ ፡ ሥጋ ፣ ለመድ
ኃኒተ ፡ ነፍስ ፡ ይሆንላቸዋል ፣
ማየ ፡ አይኅ ፡ አያገኘንም ፡
ብለው ፡ ኃጢአት ፡ ለሚሠሩ ፣
ጣኦት ፡ ለሚያመልኩ ፡ ለሞተ
ሥጋ ፡ ለሞተ ፡ ነፍስ ፡ ይሆን
ባቸዋል ።

፵፩ ፤ ወኢይሬእዩ ፡ ወኢየአምኑ ፡
ከመ ፡ ይትመየጡ ፡ እሙንቱ ፡ ማያት ።

እሊህ ፡ ውሆች ፡ በሥጋ ፡ እንዳ
ስጨነቋቸው ፡ በነፍስም ፡ እንዲ
ያስጨንቋቸው ፡ አያምኑም ፡
አያውቁም ።

ወይከውኑ ፡ እሳተ ፡ ዘይነድድ ፡ ለዓለም ።

ለዘለዓለም ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡
እንዲሆኑባቸው ፡ አያምኑም ።

፵፪ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ወሀበኒ ፡
ትእምርተ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡዓት ፡ በመ
ጽሐፍ ፡ እምሔውየ ፡ ሄኖክ ።

ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፣
የተሠወሩ ፡ የምሥጢራትን ፡
ሁሉ ፡ ምልክት ፡ አያቴ ፡ ሄኖክ ፡
በመጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ ሰጠኝ ።

ወምሳሊያተ ፡ ዘተውህባ ፡ ሎቱ ፣

ለእርሱ ፡ የተሰጡትን ፡ ምሳሌ ፡
ነገር ፡ ጽፎ ፡ ሰጠኝ ።

ወደመሮሙ ፡ ሊተ ፡ በነገረ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ዘምሳሌ ፣

የእኔ ፡ ነገር ፡ ከተጻፈበት ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ጋራ ፡ የእርሱን ፡ ነገር ፡

አንድ : አድርጎ : ሰጠኝ ፤ ይህስ፡ ባለቤቱ : ሄኖክ : ነው : ብሎ ፤ የእርሱ : መጽሐፍ : ከተጻፈበት መጽሐፍ : የእኔን : ምሳሌ : አንድ : አድርጎ : ጽፎ : ሰጠኝ፤ በዓመት : ሐምስቱ : ምዕት : ካለው : ጀምሮ : ኖኅ : ተናግሮ ታል ፡፡

## ምዕራፍ ፲፱

### ጉባኤ

፩ ፤ ወበይእቲ : ዕለት : አውሥአ : ቅዱስ : ሚካኤል : እንዘ : ይብል : ለሩፋኤል : ኃይሉ : ለመንፈስ : ይመሥጠኒ ፤

በዚያችም : ቀን : ቅዱስ : ሚካኤል : የመንፈስ : ቅዱስ : ግብሩ : ዕውቀቱ : ወደኃዘን : ይወስደኛል ፤

ወያምዕዐኒ ፤

ያበሳጨኛል : ብሎ : ለቅዱስ : ሩፋኤል : መለሰለት : ለሰው : ማዘኑ : መንፈስ : ቅዱስ : ቢያድርበት : ነውና ፤

፪ ፤ ወበእንተ : ዕፀቡ : ለኵነኔ : እንተ : ኀቡዓት : ለኵነኔ : መላእክት፤

ለደቂቀ : ሴት : ልትሆን : ስለ ተሰወረችው : መቻያ : ጭንቅ ነት : ያበሳጨኛል ፤

፫ ፤ መኑ : ውእቱ : ዘይክል : ተዓግሦተ : ዕፀቡ : ለእንተ : ተገብረት : ኵነኔ : ወነበረት ፤

በደቂቀ : ሴት : ጸንታ : የምት ኖር ፤ ለደቂቀ : ሴት : መቻያ፡ ልትሆን : የመቻያዪነቱን : ጭን ቅነት : መታገሥ : የሚቻለው : ማነው ፤ ዕፀቡ : ካለ : ለእንተ : ተገብረ : ለእንተ : ተገብረትም : ካለ ፤ ዕፀባ : ባለ : በቀና : ነበር ፤

ወይትመሰዉ : በቅድሜሃ ፤

በዚች : በመከራዪቱ : ፊት : እን ደሰም : ይቀልጣሉ ፤

፬ ፤ ወአውሥአ : ካዕበ : ወይቤሎ : ቅዱስ : ሚካኤል : ለሩፋኤል : መኑ ውእቱ : ዘኢያረጎርጎ : ልበ : ዲቤሃ ፤

ዳግመኛ : ቅዱስ : ሚካኤል : ሩፋኤልን : በዚህች : በማየ : አይኅ፡ መምጣት : ልቡን : የማያራራ : ማነው ? ብሎ : መለሰለት ፤

፭ ፤ ወኢይትሐወክ : ኵልያቲሁ : እምዛቲ ቃል ፤

ማየ : አይኅ : ትምጣ : ከማለቱ የተነሣ : ኵላሊቱ : የማይታወክ በት : ማነው ? አንድም : ዘያረ ጎርጎ : ወይትሐወክ : መሐሪ : ወመስተሣህል ፤ እርሱ : ይጥፋ : ቢል : ልቦናውን : የሚያራራ ፤ ኵላሊቱን : የሚያውክ : ማነው? አንድም : አውሥአ : ቅዱስ : ሩፋኤል : ለቅዱስ : ሚካኤል : ይላል ፤ መኑ : ዘኢያረጎርኃ : ወዘኢየሐውክ ፤ ማየ : አይኅ :

ትምጣ ፡ ከማለቱ ፡ የተነሣ ፡ ልቡን ፡ የማያራራ ፣ ኵላሊቱን ፡ የማያውክ ፡ ማነው ? ዘኢያረኃርኅን ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፣ ዘያረኃርኅን ፡ ለቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ይሰጧል ።

ኵነኔ፡ ወፅአት ፡ ዲቤሆሙ ።

መቻያ ፡ በደቂቀ ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ ወጣች ።

እምኔሆሙ ፡ ዘአውፅእዎሙ ፡ ከመዝ፤ አሁን ፡ እንደ ፡ ተናገርኩት ፡ መከራውን ፡ ከራሳቸው ፡ ያመጡት ፡ ነው ፣ መከራ ፡ ከራሱ ፡ ነውና ፡ የሚመጣ ።

፯ ። ወኮነ ፡ ሶበ ፡ ቆመ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ፡ መናፍስት ፡ ከመዝ ፡ ይቤሎ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለሩፋኤል ።

ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት፡ ለመማለድ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ሩፋኤልን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

ወኢይከውን ፡ ሎሙ ፡ ምሕረት ፡ በውስተ ፡ ዓይነ ፡ እግዚእ ።

በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ምሕረት ፡ አይደረግላቸውም ።

እስመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ተምዖሙ ።

የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ተቈጥቷቸዋልና ፡ ይቅርታ ፡ አይደረግላቸውም ፡ አለ ።

፰ ። እስመ ፡ በአምሳለ ፡ እግዚእ ፡ ይገብሩ ፡ በእንተ ፡ ዘይመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ።

መቻያ ፡ የሚመጣባቸው ፡ ስለሆኑ ፡ በጌታ ፡ አምሳል ፡ ጣዖት ይሠራሉና ። ወኢይከውን ፡ ሎሙ፡ ላለው ፡ ይሰጧል ። አንድም ፡ በእንተዝ ፡ ይመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ይላል ፡ ጣዖት ፡ ስለሠሩ ፡ መቻያ ፡ ይመጣባቸዋል ፡

ኵነኔ ፡ ዘኅቡዕ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፣ ለዘለዓለሙ ፡ የተሠወረ ፡ መቻያ ፡ ይመጣባቸዋል ።

፱ ። እስመ ፡ ኢመልአክ ፡ ወኢሰብእ ፡ ኢይትሜጠዉ ፡ መክፈልቶሙ ።

መልአክም ፡ ሁኖ ፣ ሰውም ፡ ሁኖ ፣ ጻድቅም ፡ ሁኖ ፣ መቻያውን ፡ የሚቀበል ፡ የለምና ።

አላ ፡ እሙንቱ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ተመጠዉ ፡ ኵነኔሆሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም። እነሳቸው ፡ ብቻ ፡ መቻያቸውን ለዘለዓለሙ ፡ ይቀበላሉ ፡ እንጂ ።

፲ ። ወእምድኅረዝ ፡ ኵነኔ ፣

የሥጋውን ፡ መከራ ፡ ከተቀበሉ በኋላ ።

ያደነግፅዎሙ ፡ ወያምዕዕዎሙ ።

አጋንንት ፡ በነፍስ ፡ ያስደነግጧቸዋል ። ያሳዝኗቸዋል ።

እስመ ፡ ዛተ ፡ ኵነኔ ፡ አርአዩ ፡ ለእለ የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ።

ይህችን ፡ ምሥጢረ ፡ ኃጣውእን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሰው ሁሉ ፡ አስተምረዋልና ፤

፲ ፤ ወነዋ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለአልክቱ ፡ መላእክት ፤

የደቂቀ ፡ ሴት ፡ አለቆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አስማቲሆሙ ፤

የአጋንንት ፡ አለቆች ፡ ስማቸው ይህ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሁለት፡ አርስት ፡ ነው ፤ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ፤

፲፩ ፤ ቀዳማየ ፡ ዚአሆሙ ፡ ስምያዛ ፤ (ስማዝያ)

ለአንዱ ፡ አርእስት ፡ አመጣ ፤ የአለቃው፡ አለቃ ፡ መጀመሪያው አለቃ ፡ ስምያዛ ፡ (ስማዝያ) ፡ ነው ፤

ወካልኡ ፡ አርስጢቁፋ ፤

ሁለተኛው ፡ አርስጢቁፋ ፡ ይባላል ፤

ወሣልሱ ፡ አርሚን ፤

ሦስተኛውም ፡ አርሚን ፡ ነው ፡

ወራብዑ ፡ ኮከብኤል ፤

አራተኛውም ፡ ኮከብኤል ፡ ይባላል ፤

፲፪ ፤ ወሐምሱ ፡ ጡርኤል ፤

አምስተኛውም ፡ ጡርኤል ፡ ነው ፤

ወሳድሱ ፡ ሩምያል ፤

ስድስተኛውም ፡ ሩምያል ፡ ነው ፤

ወሳብዑ ፡ ዳንኤል ፤

ሰባተኛው ፡ ዳንኤል ፡ ይባላል ፤

ወሳምን ፡ ኑቃኤል ፤

ስምንተኛውም፡ኑቃኤል፡ ነው ፤

ወታስዕ ፡ በራቅኤል ፤

ዘጠነኛውም ፡ በራቅኤል፡ ነው፤

ወዐሥር ፡ አዛዝኤል ፤

ዐሥረኛው ፡ አዛዝኤል ፡ ነው፤

ዐሥር ፡ ወአሐዱ ፡ አርማሮስ ፤

ዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ አርማሮስ ፡ ነው ፤

ዐሥር ፡ ወካልዕ ፡ በጠርያል ፤

አሥራ ፡ ሁለተኛውም ፡ በጠርያል ፡ ነው ፤

፲፫ ፤ ዐሥር ፡ ወሣልስ ፡ በሰሳኤል፤

አሥራ ፡ ሦስተኛውም ፡ በሰሳኤል ፡ ነው ፤

ዐሥር ፡ ወራብዕ ፡ አናንያል ፤

አሥራ ፡ አራተኛውም ፡ አናንኤል ፡ ይባላል ፤

ዐሥር ፡ ወሐምስ ፡ ጡርያል ፤

አሥራ ፡ አምስተኛውም ፡ ጡርያል ፡ ይባላል ፡

ዐሥር ፡ ወሳድስ ፡ ሲማሲፒኤል ፤

አሥራ ፡ ስድስተኛውም ፡ ሲማሲፒኤል ፡ ይባላል ፤

፲፬ ፤ ዐሥር ፡ ወሳብዕ ፡ ይትርኤል፤

አሥራ ፡ ሰባተኛውም ፡ ይትርኤል ፡ ይባላል ፤

ዐሥር ፡ ወሳምን ፡ ቱማኤል ፤

አሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ቱማኤል ፡ ነው ፤

አጋንንት ፡ ከዚህ ፡ ስም ፡ የተነሣ፡ ይርዱ ይንቀጠቀጡ ፡ ዘንድ ፤ በመሐላም ጊዜ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ ፡ ያንን የተሠወረ ፡ ስሙን ፡ ግለጥላቸው ፡ አለው ፤

፬ ፤ ወዝንቱ ፡ ኃይሉ ፡ ለዝ ፡ መሐላ፤ የዚህ ፡ ስም ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ነው ፤

እስመ ፡ ኃያል ፡ ውእቱ ፡ ወጽኑዕ ፤ ኃይለኛ ፡ ነውና ፡ የጸናም ፡ ነውና ፤

፭ ፤ ወአንበሮ ፡ ለዝኩ ፡ መሐላ ፤ አካዕ ፡ በእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፤

ይህን፡ ስም ፡ አካዕ ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እጅ ፡ ጻፈው ፤ ስመ መሐላ ፡ ዘጸበጠ[፩] ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቃል እንዲነገር ፡ አደረገው ፤ አካዕ ፡ ማለት ፡ አምላክ ፡ ከሃሊ ማለት ፡ ነው ፤

ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ኅቡዓቲሁ ፡ ለዝ መሐላ ፤

የዚህም ፡ ስም ፡ የተሰወሩ ፡ ምሥጢሮቹ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤

ወጽንዑ ፡ በመሐላሁ ፤

ፍጥረታቱም ፡ ሁሉ ፡ በመሐላው ፡ ጸኑ ፤

፮ ፤ ወሰማይ ፡ ተሰቅለ ፤

ሰማይ ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ጸና ፤

ዘእንበለ ፡ ይትፈጠር ፤ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ዓለም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር፡ ቃል ፡ ሰማይ ፡ ተፈጠረ ፤

ወቦቱ ፡ ምድር ፡ ተሣረረት ፡ ዲበ ፡ ማይ፤

ምድርም ፡ በእርሱ ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ ተፈጠረች ፤

፯ ፤ ወእምነ ፡ ኅቡዓተ ፡ አድባር ፡ ይመጽኡ ፡ ሳህያት ፡ ማያት ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤

ጽሩያን ፡ ማያት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ከኅቡዓን ፡ አድባር ፡ ከተራሮችም ፡ ውስጥ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ የጣፈጡ ፡ ውሃዎች ፡ ጽሩያን ፡ ማያት ፡ ይፈስሳሉ ፤ አንድም ፡ ለሕያዋን ፡ ቢል ፡ በነፍስ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ይፈስሳሉ ፤

፰ ፤ ወበውእቱ ፡ መሐላ ፡ ተፈጥረት ፡ ባሕር ፤

በዚህም ፡ ስም ፡ ባሕር ፡ ተፈጠረች ፤

ወመሠረታ ፤

ከታች ፡ ነፋስ ፤ ቀጥሎ ፡ እሳት ፤ ቀጥሎ ፡ ውሃ ፤ በዚያ ፡ ላይ ፡ መሬት ፡ አድርጎ ፡ በዚህ ፡ ቃል ተፈጠረች ፤

---

[፩]:- ደራሲ

ወርእሱሰ ፡ ለኵነኔ ፡ ተውህበ ፡ ሎቱ ለወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፤

ለአዳም ፡ ልጅ ፡ ለክርስቶስም ፡ የፍርድ ፡ ፍጻሜ ፡ ተሰጠው፤ የፍርድ ፡ ፍጻሜ ፡ ንው ፡ ኀቤየ፡ ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ማለት ፡ ነው፤

፳ ፤ ወያኀልፍ ፡ ወያማስን ፡ ኃጥአነ፡ እምገጸ ፡ ለምድር ፤

ከመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ቦታ ኃጥአንን ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ፤

ወእለ ፡ አስሐትዎ ፡ ለዓለም ፡ በሰና ስል ፡ ይትአሠሩ ፤

ሰውን ፡ ያሳቱ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትም በሰንሰለት ፡ ይታሠራሉ ፡ አለ ፤ በፍዳ ፡ ይያዛሉ ፤

፳፩ ፤ ወበማኅበሮሙ ፡ ዘሙስና ፡ ይትዐጸዉ፤

ጥፋት ፡ ሞት ፡ ባለበት ፡ ቤታ ቸው ፡ ይጋዛሉ ፤ አንድም ፡ ማኅ በሮሙ ፡ ቢል ፡ ጥፋት ፡ ሞት ፡ ወደሚስማማቸው ፡ ወገኖቻቸው ፡ ይጋዛሉ ፤

ወኵሉ ፡ ምግባሮሙ ፡ የኀልፍ ፡ እም ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ለምድር ፤

ሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ያልፋል ፤ ይጠፋል ፤

፳፪ ፤ ወእምይእዜሰ ፡ ኢይከውን ፡ ዘይማስን ፤

ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከጻድ ቃን ፡ የሚጠፋ ፡ የለም ፤ ይከ ውን ፡ ቢል ፡ የኃጥአን ፡ ወገን ፡ የሚጠፉ ፡ ይሆናሉ ፤

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ብእሲ ፡ ተርእየ ፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፤

ብእሲ ፡ ያለው ፡ አዳምን ፡ ነው ፤ ከአዳም ፡ የተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ ታይቷልና፤ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጧልና ፤

ወኵሉ ፡ እኩይ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ የኀልፍ ፤

ኃጢአት ፡ ክህደት ፡ ኃጥእ ፡ መናፍቅ ፡ ከፊቱ ፡ ይጠፋል ፤

፳፫ ፤ የሐውሩ ፡ ወይነግሩ ፡ ለውእቱ፡ ወልደ ፡ ብእሲ ፡ ወይጸንዕ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፤

ሄደውም ፡ ከአዳም ፡ ለተወለደ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳሉ ኃጢአታቸውን ፡ ይናገራሉ ፤ ማረኝ ፡ ማረኝ ፡ ይላሉ ፤ በነፍ ሳት ፡ ጌታ ፡ ፊትም ፡ ፍርዱ ፡ ይጸናል ፤

ወዝውእቱ ፡ ሣልስ ፡ ምሳሌ ፡ ዘሄ ኖክ ፤

የሄኖክ ፡ ሦስተኛ ፡ ነገሩ ፡ ይህ ነው ፤

፳፬ ፤ ወኮነ ፡ እምድኅረዝ ፡ ተለዐለ ፡ ስሙ ፡ ሕያው ፡ በኀቤሁ ፡ ለውእቱ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡ በኀበ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡

በኀቤሁና ፡ በኀበ ፡ እግዚአ ፡ መና ፍስት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ በእግዚአ ፡ ነፍሳት ፡ ዘንድ ፡

በእሊህ ፡ አዕናቍ ፡ መካከል ፡ የሕያው ፡ እሳት ፡ አንደበቶች ፡ አሉ ፤ አንድም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መካከል ፡ በመንፈስ ቅዱስ ፡ ተገልጸላቸው ፡ ብሉያ ትን ፡ ሐዲሳትን ፡ አስተምረው ፡ ከግብር ፡ ገብተው ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤

፴፯ ፤ ወርእየት ፡ መንፈስየ ፡ ዓውደ ፡ ዘየዓውዶ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ እሳት ፡ እምአርባዕቱ ፡ አጽናፊሁ ፡ ለውእቱ፡ አፍላጋት ፡ ምሉዓነ ፡ እሳት ፡ ሕያው፤

እሳት ፡ የሚከበውን ፡ ቤት ፤ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ አፍላጋት ፡ የከበቡትን ፤ እሳት ፡ የሚከበ ውን ፡ ቤት ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ እሳት ፡ የመላበትን ፡ አፍላጋት ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ የከበቡትን ፡ ቤቱን ፤ የከበበውን ፡ እሳቱን ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጸላቸው ፡ ብሉያት ፡ ሐዲሳትን ፡ አስተምረው ፡ ከግ ብር፡ ገብተው ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ጻድቃን ያሉባት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አየሁ፤

፴፰ ፤ ወየዓውድዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ በአውዱ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሱራፌል ፡ ወአፍኒን ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ኢይነውሙ ፤

ኪሩቤልና ፡ ሱራፌል ፡ አፍኒንም ፡ የዚህን ፡ ቤት ፡ ዙሪያውን ፡ ከበ ውታል ፤ እነዚህም ፡ የማያርፉ ፡ ናቸው ፤

ወየዓቅቡ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፤

የጌትነቱን ፡ ዙፋን ፡ ይጠብቃሉ፤ ጠላት ፡ ኑሮበት ፡ ማለት ፡ አይ ደለም ፤ ደጅ ፡ የሚጠኑት ፡ የሚ ከቡት ፡ ሲል ፡ ነው ፤

፴፱ ፤ ወርኢኩ ፡ መላእክተ ፡ እለ ኢይትኈለቁ ፡ አእላፈ ፡ አእላፋት ፡ ወትእልፌተ ፡ አእላፌት ፤

የማይቈጠሩ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሚ ሆኑ ፡ መላእክትን ፡ አየሁ ፤

ወየዐውድዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፤

ያንንም ፡ ቤት ፤ ይከቡታል ፤

፵ ፤ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ፤ ሩፋኤል ፡ ወፋኑኤል፤ መላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ ይበውኡ ፤ ወይወጽኡ ፡ በውእቱ ፡ ቤት ፤

በሰማያት ፡ ያሉ ፡ ቅዱሳን ፡ መላ እክት ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፤ ሩፋኤልና ፡ ፋኑኤል ፤ በዚያ ፡ ቤት ፡ ይገባሉ ፤ ይወጣሉ ፤ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ አምሳል ፡ ለተልዕኮ፤ አንድም ፡ ሰው ፡ የጸለየውን ፡ ጸሎት ፤ የሠዋውን ፡ መስዋዕት፡ ለማሣረግ ፡ የመውጣታቸው ፡ የመውረዳቸው ፡ አምሳል ፤

፵፩ ፤ ወወጽኡ ፡ እምውእቱ ፡ ቤት ፡ ሚካኤል ፡ ወገብርኤል ፤ ሩፋኤል ፡ ወፋኑኤል ፤ ወብዙኃን ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ኍልቍ ፤

የዘጠና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መጋቢ
ዎች ፡ ከሚመሯቸው ፡ ከወር ፡
መጋቢዎች ፡ ጋራ ፡ ይወጣሉ ።
ይገባሉ ። አንድም ፡ የሺሕ ፡ አለ
ቆችን ፡ የሚመሩ ፤ የወር ፡ መጋ
ቢዎች ፡ ከሚመሯቸው ፡ ከሺሕ፡
አለቆች ፡ ጋራ ፡ ይወጣሉ ፤ ይገ
ባሉ ። አንድም ፡ የዕለት፡ መጋቢ
ዎችን ፡ የሚመሩ ፤ የሺሕ ፡
አለቆች ፡ ከሚመሯቸው ፤ ከዕ
ለት ፡ መጋቢዎች ፡ ጋራ ፡ በነ
ዚህ ፡ በ፮ቱ ፡ ኀዋኅው ፡ (መስ
ኮቶች) ፡ ይወጣሉ ፤ ይገባሉ ።
፮ቱ ፡ በጽባሕ ፡ ወ፮ቱ ፡ በምዕራብ ፡
ፀሐይ ።
፮ቱ ፡ ኀዋኅው ፡ (መስኮቶች) ፡
በምሥራቅ ፤ ፮ቱ ፡ ኀዋኅው ፡
(መስኮቶች)፡በምዕራብ ፡ ናቸው።
፱ ። ወኵሎሙ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እም
ድኅረ ፡ ካልኡ ፡ ርቱዕ ።
አንዱንም ፡ አንዱን ፡ ካየሁ ፡
በኋላ ፡ ያየሁት ፡ አንዱም ፡ አን
ዱም፡ የቀና ፡ የጸና ፡ ነው።
ወመሳክው ፡ ብዙኃት ፡ እምየማኑ ፡
ወእምፀጋሙ ፡ ለዝኩ ፡ ኆኅት ፤
በዚህ ፡ ኆኅት ፡ /መስኮት/ ፡ በቀ
ኙም ፤ በግራውም ፡ ብዙ ፡ ኀዋ
ኅው ፡ /መስኮቶች/ ፡ አሉ ፤ ዝኩ
ያለው ፡ የሚያዝያን ፡ ኆኅት ፡
ነው ። ፀሐይ ፡ የተፈጠረ ፡
በሚያዝያ ፡ ኆኅት ፡ ነውና ።
እምየማኑ ፤ ወእምፀጋሙ ፡ አለ።
በቀኝ ፤ የግንቦት ፤ የሰኔ ፤ በግራ ፤
የመጋቢት ፤ የየካቲት ፤ የጥር ፤
ኆኅት ፡ አለና ።
፲ ። ወቀዳሚ ፡ ይወፅእ ፡ ብርሃን ፡
ዘየዐቢ ፡ ዘስሙ ፡ ፀሐይ ፤
ስሙ ፡ ፀሐይ ፡ የሚባል ፡ ከጨ
ረቃ ፡ የሚበልጥ ፡ ፀሐይ ፡ መጀ
መሪያ ፡ ይወጣል ።
ወክበቡ ፡ ከመ ፡ ክበበ ፡ ሰማይ ፤
ሰሌዳውም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡
ሰሌዳ ፡ ነው ።
ወኵለንታሁ ፡ ምሉዕ ፡ እሳተ ፡ ዘያበ
ርህ ፡ ወያውዒ ።
የማያበራ ፡ እሳት ፡ አለና፡ ሁለን
ተናው ፡ የሚያበራና ፡ የሚያቃ
ጥል፡ እሳት ፡ ነው ።
፲፩ ። ወሠረገላተ ፡ በኀበ ፡ የዐርግ ፡
ነፋስ ፡ ይነፍሕ ፤
ወደሠረገላው ፡ በሚወጣበት ፡
ጊዜ ፤ ነፋስ ፡ ይነፍሳል ። ሠረ
ገላ ፡ የሚለው ፡ ርጉዕ ፡ ነፋስን ፡
ነው ። ይነፍሕ፡የሚለው፡ዝርው፡
ነፋስን፡ነው ፤ ሠረገ ላውን፡የሚ
ያፋጥን፡ነው ፤ አድማስን፡በምሥ
ራቅ ፡ ከ፮ ላይ፤ በምዕራብ፡ ከ፮ ፡
ላይ ፡ ቀዶታል።
፲፪ ። ወየዐርብ ፡ ፀሐይ ፡ እምሰማይ ፡
ወይገብእ ፡ እንተ ፡ መስዕ ፤

ሠላሳ ፡ ቀን ፡ በምሥራቅ ፡ ወዳ ለችው ፡ ወደ ፡ አምስተኛዪቱ ፡ ደጃፍ ፡ ይመላለሳል ፤

ወይወፅአ ፡ እምኔሃ ፡ ወየዐርብ ፡ ውስተ ፡ ሐምስት ፡ ኆኅት ፤

ከእርሷም ፡ ወጥቶ ፡ በአምስተኛ ዪቱ ፡ ደጃፍ ፡ ይገባል ፤ ኆኅት ፡ ይለወጣል ፤ ኆኅትም ፡ የግንቦት ፡ ብተትም ፡ የግንቦት ፡ ነው ፤

፳፱ ፤ ወአሜሃ ፡ ትነውኅ ፡ ዕለት፡ ፱ተ ፡ እደ ፤

የግንቦት ፡ ዕለት ፡ ከመጋቢት ፡ ዕለት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ትበልጣ ለች ፤

ወትከውን ፡ ዕለት ፡ ዐሠርተ ፡ ወአ ሐደ ፡ ክፍለ ፤

ቀኒቱም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍ ልን ፡ ትሆናለች ፤

ወተሐጽር ፡ ሌሊት ፡ ወትከውን ፡ ፯ተ ፡ ክፍለ ፤

ሌሊቲቱም ፡ ታጥራለች ፤ ሰባት ፡ ክፍልንም ፡ ትሆናለች ፤

፴ ፤ ወይገብእ ፡ ፀሐይ ፡ ለጽባሕ ፤ ፀሐይም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ፤

ወይበውእ ፡ ውስተ ፡ ሳድስት ፡ ኆኅት ፤ ወደስድስተኛዪቱም ፡ ደጃፍ ፡ ይገ ባል ፤ ኆኅት ፡ ይለውጣል ፤ ኆኅ ትም ፡ የሰኔ ፤ ብተትም ፡ የሰኔ ነው ፤ በሰኔ ፡ በስድስተኛው ፡ ኆኅት ፡ ይወጣል ፤

ወይወፅአ ፡ ወየዐርብ ፡ በሳድስት ፡ ኆኅት ፡ ፴ ፡ ወ፩ደ ፡ ጽባሐ ፤

ሚያዝያ ፤ ግንቦት ፤ ሰኔ ፤ ሲያ ልቅ ፡ አንድ ፡ ጳጕሜን ፡ አለ ችና ፤

በእንተ ፡ ትእምርተ ፡ ዚአሃ ፤

የጳጕሜን ፡ ቀን ፡ ከእርሷ ፡ ጋራ፡ ስለኖረች ፤ በስድስተኛዪቱ ፡ ደጃፍ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይወጣል ፤ ይገባል ፤

፴፩ ፤ ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ትነውኅ ፡ ዕለት ፡ እምሌሊት ፤

በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቀኒቱ ፡ ከሌ ሊቲቱ ፡ ትረዝማለች ፤

ወትከውን፡ ዕለት ፡ ካዕበተ ፡ ሌሊት ፤

ቀኒቱም ፡ የሌሊቲቱ ፡ እጥፍ ፡ ትሆናለች፤

ወትከውን፡ ዕለት ፡ ፲ተወ፪ተ ፡ ክፍለ ፤

ቀኒቱም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍልን ፡ ትሆናለች ፤

ወተሐጽር ፡ ሌሊት ፡ ወትከውን ፡ ስድስተ ፡ ክፍለ፤

ሌሊቲቱም ፡ አጥራ ፡ ስድስት ፡ ክፍልን ፡ ትሆናለች ፤

፴፪ ፤ ወይትነሣእ ፡ ፀሐይ ፡ ከመ ፡ ትሕጽር ፡ ዕለት ፡ ወትኑኅ ፡ ሌሊት፤ ይትመየጥ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቀኑ ፡ ያጥር ፡ ዘንድ ፤ ሌሊቲቱ ፡ ትረዝም፡ ዘንድ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ይመለሳል ፤ ማለት፡ ዓውዱን ፡ ይለውጣል ፤

፲፭ ። ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ትነውኅ ፡ ሌሊት ፡ እምሌሊት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ጽባሕ ። ወተሐጽር ፡ ዕለት ፡ እምዕለት ፡ እስከ ሠላሳ ፡ ዕለት ።

በዚህችም ፡ ቀን ፡ አንዲቱ ፡ ሌሊት ፡ ከአንዲቱ ፡ ሌሊት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ትበልጣለች ። አንዲቱም ፡ ቀን ፡ ከአንዲቱ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ታጥራለች ።

ወይከውን ፡ ሌሊት ፡ ዐሠርተ ፡ ክፍለ ጥንቁቀ ፡ ወመዓልት ፡ ሰመንተ ፡ ክፍለ ።

ጠንቅቆ ፡ ቢቆጥሩት ፡ ሌሊቱም ዐሥር ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ። ቀኑም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ። የጥቅምት ፡ ሌሊት ፡ ከመስከረም ፡ ሌሊት ፡ ትበልጣለች ። አንድም ፡ ከነሐሴ ፡ ሌሊት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ትበልጣለች ።

፲፮ ። ወይወፅእ ፡ ፀሐይ ፡ እምይእቲ ፡ ሣልስት ፡ ኆኅት ።

ፀሐይም ፡ ከዚያች ፡ ከሦስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ወጥቶ ።

ወየዐርብ ፡ በሣልስት ፡ ኆኅት ። ወየዐርብ ፡ ወይገብእ ፡ ውስተ ፡ ምሥራቅ ።

በምዕራብ ፡ ባለ ፡ በሦስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ይገባል ። ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ይመለሳል ።

፲፯ ። ወይወፅእ ፡ ፀሐይ ፡ ውስተ ፡ ካልዕት ፡ ኆኅት ፡ እምሥራቅ ፡ ሠላሳ ፡ ጽባሐ ።

ፀሐይም ፡ በሁለተኛው ፡ መስኮት ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ከምሥራቅ ፡ ይወጣል ።

ኆኅት ፡ ይለወጣል ። ብተት ፡ የኅዳር ። ኆኅት ፡ የየካቲት ። መተካከል ፡ ከጥር ።

ወይገብእ ፡ በምሥራቅ ።

ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ።

፲፰ ። ወከመዝ ፡ የዐርብ ፡ በካልእ ፡ ኆኅት ፡ በምዕራብ ፡ ሰማይ ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ በሁለተኛው ፡ መስኮት ፡ በሰማይ ፡ ባለ ፡ መግቢያው ፡ ይገባል ።

ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ትከውን ፡ ሌሊት ዐሠርተ ፡ ወአሐደ ፡ ክፍለ ፡ ወዕለት ሰብዓተ ፡ ክፍለ ።

በዚያችም ፡ ቀን ፡ ሌሊቲቱ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍልን ። ቀኒቱም ፡ ሰባት ፡ ክፍልን ፡ ትሆናለች ።

፲፱ ። ወይወፅእ ፡ ፀሐይ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ እምይእቲ ፡ ካልዕት ፡ ኆኅት ወየዐርብ ፡ በምዕራብ ፡ በካልዕት ፡ ኆኅት ።

ፀሐይም ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ ከዚህች ፡ ከሁለተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ወጥቶ ፡ በሁለተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ይገባል ።

ተንባላት ፡ ይበድላሉ ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ብርሃናት ፡ ይትቀነዩ ፡ በጽድቅ ፡ በምንባረ ፡ ዓለም ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ በእውነት ፡ ያበራሉና ፡ ምንም ፡ ቢያበሩ ፡ ሰዎች ፡ የሉም ፡ ብለው ፡ ይበድላሉ ፤

፭ ፤ ፩ዱ ፡ በቀዳሚት ፡ ኖኅት ፤

አንዱ ፡ በመጀመሪያው ፡ መስኮት ፡ በጥቅምት ፤ በኅዳር ፤ በታኅሣሥ ፡ ኖኅት ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣልስት ፡ ኖኅት ፤

አንዱ ፡ በሦስተኛው ፡ መስኮት ፡ በጥር ፤ በየካቲት ፤ በመጋቢት ፤

ወ፩ዱ ፡ በራብዕት ፡ ኖኅት ፤

አንዱ ፡ በአራተኛው ፡ መስኮት ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ በመስከረም ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣድስት ፡ ኖኅት ፤

አንዱ ፡ በስድስተኛው ፡ መስኮት ፡ በሚያዝያ ፡ በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ ኖኅት ፡ (መስኮት) ፡ ይወጣል ፤

ወይትፌጸም ፡ ጥንቃቄ ፡ ዓለም ፤

ጉልቄ ፡ ዓለም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበትን ፡ ቀን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቢቆጥሩት ፤

በበሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወስሳ ፡ ወረቡዕ ምንባረ ፡ ዓለም ፤

ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ በ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ የዓለም ፡ ቁጥር ፡ ይፈጸማል ፤

፮ ፤ እስመ ፡ ለትእምርት ፤

ለጳጉሜን ፤

ወለአዝማን ፤

ለ፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤

ወለዓመታት ፤

ለ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፤

ወለመዋዕል ፡ አርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡ መልአክ ፤

ለ፬ቱ ፡ ዕለታት ፡ ተሹሟልና ፡ መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤

አንድም ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኮከብ ተሹሟልና ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤

ዘአንበሮ ፡ እግዚአ ፡ ስብሐት ፡ ዘለዓለም ፤

ዘሤሞ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ የሾመው ፤

ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡ ብርሃናተ ፡ ሰማይ ፤

በሰማይ ፡ ባሉ ፡ በፀሐይ ፡ በጨረቃ ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፤

፯ ፤ ወበዓለም ፡ ከመ ፡ ይምልኩ ፡ በገጸ ፡ ሰማይ ፤

በሰማይ ፤ በምድር ፤ ያበሩ ፡ ዘንድ ፤

ወይትረአዩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤

ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ይመግቡ ፡ ዘንድ ፤

፰ ፤ ወይኩኑ ፡ መራሕያነ ፡ ለመዓልት ፡ ወለሌሊት ፡ ፀሐይ ፡ ወወርኅ ፡ ወከዋክብት ፤

ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ነፋሳት ፡ እለ ፡ መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ ፬ቱ ፡ በቀዳ ሚት ፡ ኖኅት ፡ ሲል ፡ ነው ፤
እሊህን ፡ አራቱን ፡ ነፋሳት ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ፬ኛ ፡ መዓዝን ፡ በሚሆን ፡ በምዕራብ ፡ ካሉ ፡ ኀዋ ኀው ፡ በመጀመሪያዪቱ ፡ ኖኅት ፡ በመስዕ ፡ በኩል ፡ በምትሆን ፤
እምኔሃ ፡ ይወፅእ ፡ ጠል ፡ ወዝናም ፡ ወአስሐትያ ፡ ወቍር ፡ ወሐመዳ ፡ ወደደክ ፤
ከእርሷ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፣ ክፉ ፡ ዝናም ፣ የረጋው ፡ የተበተነው ፡ ውርጭ ፣ ዋግ ፣ ቀቅ ፡ ይወጣል ፤
፲፯ ፤ ወእምነ ፡ ኖኅት ፡ ማእከ ላይት ፡ ይወፅእ ፡ ጠል ፡ ወዝናም ፡ ሰላም ፡ ወበረከት ፤
ከመካከለኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ በጎ ፡ ጠል ፣ በጎ ፡ ዝናም ፣ ፍቅር ፣ በረከትም ፡ ይወጣል ፤
፲፯ ፤ ወበደኃሪት ፡ ኖኅት ፡ እንተ ፡ መንገለ ፡ አዜብ ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ የብስ ፣ ወድምሳሴ ፣ ዋዕይ ፣ ወኀጕል ፤
በአዜብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በኋለ ኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ ከእርሷ ፡ ድርቅ ፡ ጥፋት ፡ ዋዕይ ፡ ይወጣል ፤
፲፰ ፤ ወተፈጸማ ፡ ፲ሩ ፡ ወ፪ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ዘ፬ቱ ፡ ኀዋኀወ ፡ ሰማይ ፣
በ፬ቱ ፡ መዓዝነ ፡ ሰማይ ፡ ያሉ ፲፪ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ (መስኮቶች) ፡ ተፈጸሙ ፤
ወኵሉ ፡ ትእዛዞሙ ፤
የ፲፪ቱን ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዛቸውን ፡
ወኵሉ ፡ መቅሠፍቶሙ ፤
የ፰ቱ ፡ ነፋሳት ፡ መቅሠፍታቸ ውን ፤
ወኵሎ ፡ ሰላሞሙ ፡ አርአይኩከ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፤
ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ የ፬ቱን ፡ ነፋ ሳት ፡ ምሕረታቸውን ፡ ሁሉ ፣ መቅሠፍታቸውንም ፡ ሁሉ ፣ ተድላ ፡ ደስታቸውንም ፡ ሁሉ ፣ አሳየሁህ ፡ አለ ፤
፲፱ ፤ ይጼውዕዎ ፡ ለነፋስ ፡ ቀዳ ማዊ ፡ ጽባሐዊ ፡ እስመ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፤
መጀመሪያ ፡ የወጣ ፡ ነውና ፡ መጀመሪያ ፡ የወጣውን ፡ ነፋስ ፡ ስሙን ፡ ጽባሕዊ ፡ ይሉታል ፤
፳ ፤ ወይጼውዕዎ ፡ ለካልእ ፡ አዜብ፡ እስመ ፡ ልዑል ፡ ህየ ፡ ይወርድ ፡ ወፈድፋደ ፡ ህየ ፡ ይወርድ ቡሩክ ፡ ዘለዓለም ፤
ልዑል ፡ ብርሃን ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፤ አንድም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ይወርዳ ልና ፣ ደብረ ፡ ሲና ፡ ያለች ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ናትና ፡ ለካልዕ አዜብ ፡ ውዑይ ፡ ነፋስ ፡ ይወ ርዳልና ፣ ይወርድ ፡ ቡሩክ ፡ ብርሃን ፤ አንድም ፡ ጌታ ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፤

የሰውንም ፡ ገንዘብ ፡ (ከብት) ፡
ሁሉ ፡ ይበላል ፤
ወይትረዐይ ፡ ማእከለ ፡ እልኩ ፡
አልሕምት ፤
በእነዚያ ፡ ላሞች ፡ መካከል ፡
ይሰማራል ፤ ከአዋልደ ፡ ቃየል ፡
ጋራ ፡ ይኖራል ፤
፲፮ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ አልሕ
ምተ ፡ ዓቢያነ ፡ ወጸሊማነ ፤
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጥቋቁሮች ፡
ታላላቆችን ፡ ላሞች ፡ አየሁ ፤
ደቂቀ ፡ ሴትን ፤
ወናሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ወለጡ ፡ ምዕያ
ሞሙ ፤
ሕገ ፡ ስብሳባቸውን ፤
ወምርዓዮሙ ፤
ሥርዓታቸውን፡ለወጡ ፤
ወአጣዕዋሆሙ ፤
ልጅ ፡ አስወለዷቸው ፤ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ አዋልደ ፡ ቃየልን ፡ ኃጢ
አት ፡ አሠሯቸው ፤
፲፯ ፤ ወአኀዙ ፡ የአወይዉ ፡ ፩ዱ ፡
ምስለ ፡ ካልኡ ፤
አንዱም ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ አዋ
ልደ ፡ ቃየል ፡ ይጮኹ ፡ጀመር ፤
ወካዕበ ፡ ርኢኩ ፡ በራእይ ፡ ወነጸ
ርክዎ ፡ ለሰማይ ፤
ዳግመኛም ፡ በራእይ ፡ ደብር ፡
ቅዱስን ፡ አየሁት ፤
፲፰ ፤ ወነዋ ፡ ርኢኩ ፡ ከዋክብተ ፡
ብዙኃነ ፡ ወወረዱ ፤
እነሆ ፡ ብዙ ፡ ኮከቦችን ፡ አየሁ ፤
ወረዱም ፤ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከደብር ፡
ቅዱስ ወደስምያዛ ፡ ወረዱ ፤
ወተገድፉ ፡ እምሰማይ ፡ ኀበ ፡ ዝኩ ፡
ኮከብ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወማእከለ ፡ እልኩ፡
ጣዕዋ ፤
ወደዚያ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡
ኮከብ ፡ ወረዱ ፤ በእነዚያም ፡
ጥጆች ፡ መካከል ፡ ተጣሉ ፤ ወደ ፡
ስምያዛ ፡ ወደ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፤
፲፱ ፤ ወአልሕምት ፡ ኮኑ ፡ ምስሌ
ሆሙ ፡ ይትረዐዩ ፡ ማእከሎሙ ፤
ላሞችም ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ በመካ
ከላቸው ፡ የሚሠማሩ ፡ ሆኑ ፤
ማለት ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከአዋ
ልደ ፡ ቃየል ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡
ጀመረ ፤
ወነጸርክዎሙ ፡ ወርኢኩ ፤
እነሱንም ፡ ፈጽሜ ፡ አየኋቸው ፤
፳ ፤ ወነዋ ፡ ኵሎሙ ፡ አውፅኡ ፡
ኀፍረታቲሆሙ ፡ ከመ ፡ አፍራስ ፤
እነሆ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ፈረ
ሶች ፡ ኀፍረታቸውን ፡ አውጥ
ተው ፤
ወአኀዙ ፡ ይዕርጉ ፡ ዲበ ፡ ዕጓላተ ፡
አልሕምት ፤
በላሞች ፡ ጊደሮች ፡ ላይ ፡ ይንጠላ
ጠሉ ፡ ጀመር ፤ ማለት ፡ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ እንደ ፡ አለሌ ፤ አዋልደ ፡
ቃየል ፡ እንደባዝራ ፡ ሁነው ፡
ይንጠላጠሉባቸው ፡ ጀመረ ፤

ቈናጽል ።
አማሌቃውያን ።
ወግሔያት ።
ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ።
፫ ፡ ወሐንዘር ።
አነር ። (ያልታወቁ ፡ አሕዛብ) ።
ወሲሲት ፡ ወአንሥርት ።
ውዳቂ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ።
ወአውስት ።
ዘማች ፡ አሞራ ።
ወሆባይ ።
አንጭት ፡ አሞራ ።
ወፎንቃስ ።
ጉሬዛ ። እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ናቸው ።
ወቋዓት ።
ሮማውያን ፡ ሁሉ ፡ ከእነዚህ ፡ ተወለዱ ።
፬ ፡ ወተወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ላሕም ፀዓዳ ።
በመካከላቸው ፡ ላም ፡ ተወለደ ፡ አለ ። ባለአእምሮ ፡ አብርሃም ፡ በመካከላቸው ፡ ተወለደ ።
ወአንዙ ፡ ይትናሰኩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ።
አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ጀመር ።
፭ ፡ ወዝኩ ፡ ላሕም ፡ ፀዓዳ ፡ ዘተወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ወለደ ፡ አድገ ፡ ገዳም ።
በመካከላቸው ፡ የተወለደው ፡ ያ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አድግ ፡ ወለደ ፡ አለ ። በመካከላቸውም ፡ የተወለደ ፡ ባለአእምሮ ፡ የሚሆን ፡ አብርሃም ፡ እስማኤልን፡ ወለደ ።
ወላሕመ ፡ ፀዓዳ ፡ ምስሌሁ ።
እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ ወለደ ፡ አለ ። እንደርሱም ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ።
፮ ፡ ወበዝኀ ፡ አዕዱገ ፡ ገዳም ።
አዕዱገ ፡ ገዳም ፡ በዙ ፡ አለ ። የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ በዙ ። ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወልዷልና ።
ወውእቱ ፡ ላሕም ፡ ዘተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ወለደ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ጸሊመ ።
ከእርሱ ፡ የተወለደ ፡ ያ ፡ ላም ፡ ጥቁር ፡ እርያን ፡ ወለደ ። ከአብርሃም ፡ የተወለደ ፡ ይስሐቅ ። አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ኤሳውን ፡ ወለደ ።
ወበግዐ ፡ ፀዓዳ ።
ነጭ ፡ በግንም ፡ ወለደ ፡ አለ ። ባለ ፡ አእምሮ ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ።
፯ ፡ ወውእቱ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ፡ ወለደ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕርወ ።
ያም ፡ እርያ ፡ ብዙ ፡ እርያዎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ። ኤሳው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወለደ ። የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ወውእቱ ፡ በግዕ ፡ ወለደ ፡ አሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ አባግዐ ፤

ያም ፡ በግ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ በጎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ፣ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ያዕቆብ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ ወለደ ፤

፰ ፤ ወሶበ ፡ ልሕቁ ፡ እሙንቱ ፡ አሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አባግዕ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ መጠውዎ ፡ ለአዕዱግ ፡ ገዳም ፤

እኒያ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በጎችም፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱን ፡ ለአዕዱግ ፡ ገዳም ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡት ፡ አለ ፣ እነዚህ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ እስራኤልም ፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ዮሴፍን ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ለ፳ብር ፡ ሸጡት ፤

፱ ፤ ወእልኩ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡ ካዕበ ፡ መጠውዎ ፡ ለዝኩ ፡ በግዕ ፡ ለአዝእብት ፣

እኒያ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡ ያን ፡ በግ ፡ ለአዝብዕት ፡ ሰጡት ፡ አለ ፣ እነዚህም ፡ እስማኤላውያን ፡ ዳግመኛ ፡ ዮሴፍን ፡ ለግብፃውያን ፡ ለ፴ ፡ ብር ፡ ሸጡት ፤

ወልህቀ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ማዕከለ ፡ አዝእብት ፤

ያም ፡ በግ ፡ በአዝብዕት ፡ መካከል ፡ አደገ ፡ አለ ፣ ዮሴፍ ፡ በግብጻውያን ፡ መካከል ፡ አደገ ፤

፲ ፤ ወእግዚእ ፡ አምጽአሙ ፡ ለአሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ አባግዕ ፡ ከመ ፡ ይኅድሩ ፡ ምስሌሁ ፤

ጌታው ፡ ዐሥራ ፡ አንዱን ፡ በጎች፡ ከእርሱ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አመጣቸው ፡ አለ ፣ አሥራ ፡ አንዱ ፡ ወንድሞቹን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አመጣቸው ፤

ወይትረዐዩ ፡ ምስሌሁ ፡ ማዕከለ ፡ አዝዕብት ፤

በግብጻውያንም ፡ መካከል ፡ ከሱ ጋር ፡ አብረው ፡ ይሠማሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ አመጣቸው ፤

፲፩ ፤ ወበዝኁ ፡ ወኮኑ ፡ መራዕየ ፡ ብዙኃነ ፡ ዘአባግዕ ፣

እነርሱም ፡ ብዙ ፡ የበጎች ፡ መንጋ፡ ሆኑ ፡ አለ ፣ እነዚህ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ልጅነት ፣ ወገንነት ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ፤

ወወጠኑ ፡ አዝዕብት ፡ እንዘ ፡ ያፈርህዎሙ ፡ ወአጠወቅዎሙ ፡ እስከ ፡ የኃልቁ ፡ ደቂቆሙ ፤

ግብጻውያን ፡ ጡቡን ፡ እያሠሩ ፡ እያስረገጡ ፡ ኖራ ፡ እያስወቀጡ ፡

የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ እየመራቸው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሄደ ።

ወኵሎሙ ፡ አባግዒሁ ፡ ተለውዎ ፤

እስራኤልም ፡ ሁሉ ፣ ቀን ፡ ዓምደ፡ ደመናውን ፣ ሌሊት ፡ ዓምደ ፡ እሳቱን ፡ እያዩ ፡ ይከተሉት ፡ ነበር ።

ወገጹ ፡ ስቡሕ ፤

ፊቱ ፡ ብሩህ ፡ ነው ።

ወግሩም ፡ ራእዩ ፡ ወክቡር ፣

በባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ የከበረ ፡ ነው ፣ ያየዋልና ፡ ስቡሕ ፡ ክቡር ፡ ግሩም ፡ አለ ።

፳፬ ፤ ወአዝእብትሰ ፡ አኀዙ ፡ ይትልውዎሙ ፡ ለእልኩ ፡ አባግዐ ፡ እስከ ፡ ተራከብዎሙ ፡ በአሐቲ ፡ አይገ ፡ ማይ ፤

ግብፃውያን ፡ ግን ፡ በአንዲት ፡ ኤርትራ ፡ በተጠራቀመች ፡ ውሀ ፡ እስኪገናኟቸው ፡ ድረስ ፡ እኒህ ፡ እስራኤልን ፡ ይከተሏቸው ፡ ጀመር ።

፳፭ ፤ ወውእቱ ፡ አይገ ፡ ማይ ፡ ተሰጠ ፤

ያም ፡ የተጠራቀመ ፡ ውሀ ፡ ከሦስት ፡ ከአራት ፡ ተከፈለ ።

ወቆመ ፡ ማይ ፡ እምዝየ ፡ ወእምዝየ በቅድመ ፡ ገጸሙ ፤

ውሀውም ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ተከፍሎ በፊታቸው ፡ ጸና ።

ወእግዚኦሙ ፡ ለአባግዐ ፡ ይመርሖሙ ፣

የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ።

ወቆመ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ አዝዕብት ፤

በግብጻውያንና ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ይሔድ ፡ የነበረው ፡ ደመና፡ እስራኤል ፡ ግብጻውያንን ፡ አይተው ፡ ቢፈሩ ፡ ደመናውን ፡ መልሶ፡ ከመካከላቸው ፡ ጋርዶታልና ።

፳፮ ፤ ወዓዲሆሙ ፡ እልኩ ፡ አዝእብት ፡ ኢርእይዎሙ ፡ ለአባግዐ ፤

ዳግመኛ ፡ ግብጻውያን ፡ ፳ኤልን አላዩዋቸውም ።

ወሖሩ ፡ ማእከለ ፡ ዝኩ ፡ አይገ፡ ማይ ፤

በዚህ ፡ በተጠራቀመውም ፡ ውሃ መካከል ፡ ሄዱ ።

፳፯ ፤ ወአዝእብት ፡ ተለውዎሙ ፡ ለአባግዐ ፤

ግብፃውያንም ፡ እስራኤልን ፡ ተከተሏቸው ።

ወሮጹ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ እልክቱ ፡ አዝእብት ፡ በዝኩ ፡ አይገ ፡ ማይ ፤

ያገራችን ፡ ውሀ ፡ ፳ኤልን ፡ ያሳሰጠመች ፡ እኛን ፡ ታሰጥማለችን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ውሀው ፡ ሮጡ ።

፳፰ ፤ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለእግዚኦሙ ፡ ለአባግዐ ፡ ገብኡ ፡ ከመ ፡ ይጕየዩ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

ወእምዝ ፡ ርኢክዎ ፡ ለእግዚእ ፡ አባ
ግዕ ፡ ዘቆመ ፡ ቅድሜሆሙ ፡፡
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በፊታቸው ፡
የቆመ ፡ የእስራኤልን ፡ ጌታ ፡
አየሁት ፡፡
፴፭ ፡ ወራእዩ ፡ ዓቢይ ፡ ወግሩም ፡
ወኃያል ፡፡
መልኩም ፡ ያማረ ፡ የሚያስ
ፈራ ፡ ኃይለኛም ፡ ነው ፡፡
ወኵሎሙ ፡ እልኩ ፡ አባግዕ ፡ ርእ
ይዎ ፡ ወፈርህዎ ፡ እምገጹ ፡፡
ኢይትናገረነ ፡ እግዚአብሔር ፡
አላ ፡ ይትናገረነ ፡ ሙሴ ፡ ማለ
ታቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡፡ እኒ
ህም ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ እርሱን፡
አይተው ፡ ፊቱ ፡ ከመገለጡ ፡
የተነሣ ፡ ፈሩ ፡፡
፴፮ ፡ ወኵሎሙ ፡ እልክቱ ፡ ይፈ
ርህዎ ፡ ወይርዕዱ ፡ እምኔሁ ፡፡
እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡ የተ
ነሣ ፡ ፈርተው ፡ ይርዱ ፡ ይንቀ
ጠቀጡ ፡ ነበር ፡፡
ወይጸርሑ፡ድኅሬሁ ፡ ለዝኩ ፡ በግዕ ፡
ምስሌሁ ፡ ዘሀሎ ፡ ለካልእ ፡ በግዕ ፡
ዘኮነ ፡ ማእከሎሙ ፡፡
ከአሮን ፡ ጋራ ፡ ባለ ፡ በመካከል
ሁኖ ፡ በሚጠብቃቸው ፡ በሙሴ
ኋላ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፡፡ እን
ድም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አሮን ፡
በሚጠብቃቸው ፡ በሙሴ ፡ ኋላ
ይጮኹ ፡ ነበር ፡፡

፴፯ ፡ እስመ ፡ ኢንክል ፡ ቀዊመ ፡
ቅድመ ፡ እግዚእነ ፡ ወኢነጽሮቶ ፡፡
በጌታችን፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ፊቱ
ንም ፡ ማየት ፡ አይቻለንምና፡፡
እንድም ፡ ኢይክሉ ፡ ሲል ፡ ነው ፡፡
መቆም ፡ አይቻላቸውምና፡፡
ወገብአ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ዘይመርሖሙ
ወዐርገ ፡ በድማኅ ፡ ዝኩ ፡ ኰኵሕ ፡፡
የሚመራቸውም ፡ ይህ ፡ ሙሴ
ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡
ራስ ፡ ወጣ ፡፡
፴፰ ፡ ወአባግዕ ፡ አኀዙ ፡ ይጸለሉ ፡
አዕይንቲሆሙ ፡ ወይስሐቱ ፡ እምፍ
ኖት ፡ እንተ ፡ አርአዮሙ ፡፡
የእስራኤልም ፡ ዓይነ ፡ ልቡና
ዎቻቸው፡ በድንቁርና ፡ ይያዙ ፡፡
ካስተማራቸውም ፡ ሕግ ፡ ወጥ
ተው ፡ ይስቱ ፡ ጀመር ፡፡
፴፱ ፡ ወዝኩ ፡ በግዕ ፡ ኢያእመረ ፡
ወእግዚኦሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ተምዐ ፡
ዓቢየ ፡ መዓተ ፡ ዲቤሆሙ ፡፡
የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር፡
ግን ፡ በእነርሱ ፡ ታላቅ ፡ ቁጣን ፡
ተቆጣባቸው ፡ ኅድገኒ ፡ እጥስ
ዮሙ ፡ በመዓትየ[፩] ፡ እንዲል ፡፡
፵ ፡ ወአእመረ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ወወ
ረደ ፡ እምነ ፡ ድማኅ ፡ ለኰኵሕ ፡፡
ይህም ፡ ሙሴ ፡ በደላቸውን ፡
አውቆ ፡ ከደብረ ፡ ሲና ፡ ራስ
ወረደ ፡፡

---

፩ ፡ ዘፀ. ፴፪፡፲

ዘመርሖሙ : ለአባግዐ ፤
፳ኤልን : የመራቸው : የጠበቃ
ቸው : ብሎ : ለሙሴ : ቀጸለ ፤
፴፯ ፤ ወርኢኩ : እስከ : ተኀጕሉ :
ኵሉሙ : አባግዐ : ዓቢያን ፤
ስልሳው : እልፍ :አጋር : ሁሉ
እስኪጠፉ : ድረስ : ደርሼ :
አየሁ ፤
ወንዑሳን : ተንሥኡ : ህየንቴሆሙ ፤
ስለ : እበው : ፈንታ : ውሉድ
ተነሡ ፤
ወቦኡ : ውስተ : መርዔት ፤
መንጋ : ወደመሆን : ገቡ ፤ በዙ ፤
፴፰ ፤ ወቀርቡ : ኀበ : ፈለገ : ማይ ፤
ወደ : ዮርዳኖስ : ቀረቡ ፤
ወዝኩ : በግዕ : ዘይመርሖሙ ፤
የመራቸው : ባለ : አእምሮ :
የሆነው : ሙሴ ፤
ወዘኮነ : ብእሴ : ተሌለየ : እም
ኔሆሙ : ወሰከበ ፤
የጠበቃቸው : ሙሴ : በሞት
ተለየ : ዐረፈ ፤
፴፱ ፤ ወኵሉሙ : አባግዐ : ኃሠ
ሥዎ ፤
እስራኤልም : ሁሉ : ፈልገው :
አጡት ፤
ወጸርሑ : ዲቤሁ : ዓቢየ : ጽራሐ ፤
በእሱም : ሞት : ታላቅ : ጩኸ
ትን : ጮሁ : ለዚህም : ለሙሴ :
፴ : ቀን : አለቀሱ ፤

ወርኢኩ : እስከ : አርመሙ : እም
ጽራሖ : ለዝኩ : በግዕ ፤
ለዚህም : ለሙሴ : በሚጮ
ሁት : ጩኸት : ዝም : እስኪሉ :
ድረስ : ደርሼ : አየሁ ፤
፵ ፤ ወኀለፍዎ : ለዝኩ : ውኂዘ :
ማይ ፤
የዚያንም : ውሀ : ፈሳሽነት :
አልፈውት : ሄዱ ፤
ወቆሙ : አባግዕ : ኵሉሙ : እለ :
ይመርሕዎሙ : ተከሉሙ : ለእለ :
ሰከቡ : ወመርሕዎሙ ፤
ስለ : ሞቱት : ሰዎች : የሚጠ
ብቋቸው:የሙሴ:ምትክ:ኢያሱ፤
የአሮን : ምትክ : የሚሆን :
አልዓዛር : ጸኑ ፤
፵፩ ፤ ወርኢኩ : አባግዕ : እስከ :
ይበውኡ : ውስተ : መካን : ሠናይ ፤
እስራኤልም : ወአወርሰከ :
ሀገረ : እንተ : ትውኀዝ : ሀሊበ
ወመዓረ : ወደተባለች : ወደ :
ኢየሩሳሌም : እስኪገቡ : ድረስ
ደርሼ : አየሁ ፤
ወምድር : ሐዋዝ ፤
ያማረች : የተወደደች :
ወስብሕት ፤
ክብርት : ወደሆነች : ሀገር :
ውሉድ : እስኪገቡ : ድረስ :
ደርሼ : አየሁ ፤

፷፮ ፤ ወእምኔሆሙ ፡ ርኢኩ ፡ ሶበ ፡
ኀደጉ ፡ ቤቶ ፡ ለእግዚአ ፡ አባግዕ ፡
ወማኅፈዶ ፤
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ማደሪያው ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስንም ፡ በተዉ ፡ ጊዜ ፡ ከእነሱ ፡
የተነሣ ፡ የመጣባቸውን ፡ መከራ ፡
አየሁ ፤
ወእምኵሉ ፡ ስሕቱ ፡ ወተጸለለ ፡ አዕይ
ንቲሆሙ ፤
ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓት ፡ ወጥ
ተው ፡ ዓይነ ፡ ልቡናቸውም ፡ በድ
ንቁርና ፡ ተያዘ ፤
፷፯ ፤ ወርኢኩ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፡
ከመ ፡ ገብረ ፡ ቀትለ ፡ ብዙኀ ፡ ዲቤ
ሆሙ ፤
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ብዙ ፡ ሰልፍን ፡ በራሳቸው፡
ላይ ፡ እንዳደረገ ፤
በበመራዕይሆሙ ፡ እስከ ፡ ይጼውዕዎ
እልኩ ፡ አባግዕ ፡ ለዝኩ ፡ ቀትል ፤
በየወገናቸውም ፡ እነዚህ ፡ እስራ
ኤል ፡ ያንን ፡ ሰልፍ ፡ እስኪጠ
ሩት ፡ ድረስ ፡ አየሁ ፤
፷፰ ፤ ወአግብኡ ፡ መካኖ ፤
ሀገሩ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለአሕዛብ
አሳልፈው ፡ ሰጡ ፤
ወኃደጎሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ አናብስት ፤
ወአናምርት ፤ ወአዝእብት ፡ ወአጽዕ
ብት ፡ ወውስተ ፡ እደ ፡ ቈናጽል ፡
ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ፤
በፋርስ ፤ በሦርያና ፡ በግብፅ ፤
በሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ እጅና ፡
በአማሌቅ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ጣላ
ቸው ፤ በባቢሎናውያንም ፡ እጅ ፡
አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤
፷፱ ፤ ወአንዙ ፡ እልክቱ ፡ አራዊተ
ገዳም ፡ ይምሥጥዎሙ ፡ ለእልኩ ፡
አባግዕ ፤
እኒህም ፡ አሕዛብ ፡ እስራኤልን
በሞት፡ ይነጥቋቸው ፡ ጀመር ፤
ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ኀደጉ ፡ ለዝኩ ፡
ቤተ ፡ ዚአሆሙ ፤
ደብተራ ፡ ኦሪትን ፤
ወማኅፈዶሙ ፡
ቤተ ፡ መቅደስን ፡ እስከ ፡ ተዉ ፡
ድረስ ፡ አየሁ ፤
፸ ፤ ወወደዮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ውስተ ፡
እደ ፡ አናብስት ፡ ከመ ፡ ይምሥጥዎሙ ፡
ወከመ ፡ ይብልዕዎሙ ፡ ውስተ ፡
እደዊሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አራዊት ፤
በሞት ፡ ይነጥቋቸው ፡ ዘንድ ፡
በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ከብቶ
ታቸውንም ፡ ይበሉባቸው ፡ ዘንድ ፤
በሌሎች ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡
ጣላቸው ፤
፸፩ ፤ ወአነ ፡ አኀዝኩ ፡ እጽራሕ ፡
በኵሉ ፡ ኃይልየ ፤
እኔም ፡ በፍጹም ፡ ኃይሌ ፡
እጮህ ፡ ጀመር ፤
ወእጸውዖ ፡ ለእግዚአ ፡ አባግዕ ፡
ወአርኢዮ ፡ በእንተ ፡ አባግዕ ፤
የእስራኤልን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ እለምነው ፤ የእስራኤል
ንም ፡ ግፍ ፡ አሣየው ፡ ጀመርኩ ፤

ወሚመጠነ ፡ ይሜጥውዎሙ ፡ ለኃጕል ፤
ምን ፡ ያህል ፡ ለጥፋት ፡ ይሰጧቸው ፡ እንደሆነ ፤
፯ ፤ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊተ ፡ ዝንቱ ፡ ስምዐ ፡ ዲቤሆሙ ፤
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ለኔ ፡ ምስክር ፡ ይሆነኝ ፡ ዘንድ ፤
ከመ ፡ አእምር ፡ አነ ፡ ኵሎ ፡ ግብሮሙ ፡ ለኖላውያን ፤
የነገሥታቱን ፡ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ መርምሬ ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ ሊሆነኝ ጻፍ ፤
፰ ፤ ወእመጥዎሙ ፡ ወእርአይ ፡ ዘይገብሩ ፡ ለእመ ፡ ይነብሩ ፡ በትእዛዝየ ፡ ዘአዘዝክዎሙ ፡ ወእመ ፡ አልቦ ፤
በአዘዝኋቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ እንደሆነ ፤ አይኖሩም ፡ እንደሆነ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አይቼ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ጻፍ ፡ አለው ፤
፱ ፤ ወኢያእምሩ ፡ ወኢታርእዮሙ ፡ ወኢትዝልፎሙ ፤
የምትጽፍባቸውን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ አይወቁ ፤ አንተም ፡ አታሳያቸው ፡ አለ ፤
አላ ፡ ጸሐፍ ፡ ኵሎ ፡ ኃጕሎሙ ፡ ለኖላውያን ፡ በበጊዜሁ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፤
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ያንዱንም ፡ ያንዱን ፡ የነገሥታቱን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ጻፍ ፡ እንጂ ፤
ወአዕርግ ፡ ኀቤየ ፡ ኵሎ ፤
ሁሉንም ፡ ጽፈህ ፡ ወደኔ ፡ አምጣው ፡ እንጂ ፤
፲ ፤ ወርኢኩ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ እልኩ ፡ ኖላውያን ፡ ይርዐዩ ፡ በበጊዜሁ ፤
እኒህም ፡ ነገሥታቱ ፡ በየሹመታቸው ፡ እስኪጠብቋቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፤
ወአኀዙ ፡ ይቅትሉ ፡ ወያኀጕሉ ብዙኀነ ፡ እምትእዛዞሙ ፤
ከትእዛዛቸው ፡ ወጥተው ፡ ብዙ ያጠፉ ፡ ጀመር ፤ አንድም ፡ ካዘዝኋቸው ፡ አትርፈው ፡ መምህራኑን ፡ ነገሥታቱን ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ከሕዝቡ ፡ አጥፍተዋልና ፤
፲፩ ፤ ወኀደጉ ፡ እልክተ ፡ አባግዐ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ አናብስት ፤
ነገሥታቱም ፡ እኒህን ፡ እስራኤልን ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ጣሏቸው ፤
ወበልዑ ፡ ወውኅጡ ፡ መብዝኅቶሙ ፡ ለእልኩ ፡ አባግዕ ፡ አናብስት ፡ ወአናብርት ፤
የፋርስና ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎችም ከእስራኤል ፡ ብዙዎችን ፡ ፈጽመው ፡ አጠፏቸው ፤

አሕዛብ ፣ ሮማውያን ፣ እስራ
ኤልን ፡ ሐዋርያትን ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያጠፏቸው ፡
ነበር ፤ ይህም ፡ ይህ ፡ ነው ፣
ከዚህም ፡ ጋራ ፡ እስራኤልን ፡
ይማርኳቸው ፡ ነበር ፤
ወይሠርሩ፡ ዲቤሆሙ ፡ወይበልዕዎሙ፣
ፈጥነው ፡ ወደ ፡ እነርሳቸው ፡
ሄደው ፡ ያጠፏቸው ፡ ነበር ፤
፲፩ ፤ ወአባግዕሰ ፡ ያረምሙ ፡ ወዳ
ቤላት ፡ የዓወይዉ ፡ ወይጸርሑ ፤
ሐዋርያት ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡
ነበር ፣ ኋላ ፡ ግን ፡ ለእስራኤል ፡
ሐዋርያት ፡ ጩኸው ፡ አስተማሩ ፤
ወእልክቱ ፡ ቋዓት ፡ ይትጋደሉ ፡
ወይትባአሱ ፡ ምስሌሁ ፤
ሮማውያን ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡
ይጣሉ ፡ ነበር ፤
፲፪ ፤ ወፈቀዱ ፡ ያእትቱ ፡ ቀርኖ ፣
ሥልጣኑን ፡ ሊያርቁ ፡ ወደዱ ፤
ወኢክህልዎ ፤
ጌታን ፡ አልቻሉትም ፤
ወርኢክዎሙ ፡ እስከ ፡ መጽኡ ፡ ኖላ
ውያን ፡ ወአንስርት ፣
ነገሥታት ፡ የሞአብ ፣ የአሞን ፡
ሰዎች ፡
ወእልኩ ፡ አውስት ፡ ወሆባይ ፤
እነዚህ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡
እስከ ፡ መጡበት ፡ ዘመን ፡ ደርሼ ፡
አየሁ ፤ አንድም ፡ ሰብአ ፡
ሰገል ፡ እስከመጡበት ፡ ዘመን ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፣ ተራ ፡ አልፈለ
ገም ፤
፲፫ ፤ ወጸርሑ ፡ ለቋዓት ፡ ከመ
ይቀጥቅጥዎ ፡ ለቀርኑ ፡ ዝኩ ፡ ዳቤላ
የክርስቶስን ፡ ሥልጣን ፡ ያርቁ
ዘንድ ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡
ለሮማውያን ፡ እርዱን ፡ ብለው ፡
ጮኹ ፤
፲፬ ፤ ወተባአሱ ፡ ወተቃተሉ ፤
ሮማውያን ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ተጣ
ልተው ፡ ተጋደሉ ፤
ወውእቱ ፡ ይትበአስ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ወጸርሐ ፡ ከመ ፡ ትምጽእ ፡ ረድኤቱ ፣
እርሱም ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ተጣላ ፣
ለሰው ፡ የሚያደርጋት ፡ ረድኤቱ
ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ አንድም ፡
ረዳኤ ፡ ኵሉ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡
የሚለው ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤
፲፭ ፤ ወርኢኩ ፡ እስከ ፡ መጽአ ፡
ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ ዘጸሐፈ ፡ አስማቲ
ሆሙ ፡ ለኖሎት ፤
የነገሥታቱን ፣ የመምህራኑን ፡
ስም ፡ የጻፈ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል
እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፤
፲፮ ፤ ወየዐርግ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለእግዚአ ፡
አባግዕ ፤
ወደ ፡ እስራኤል ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡
እስከ ፡ ወጣ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡
አየሁ ፤

ወይትገኀሉ ፡ በመዓት ፤
በቁጣ ፡ ይጠፋሉ ፤
ወበዘኮነኒ ፡ ኃያል ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፣
ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡
በጽኑ ፡ ፍርድ ፤ አንድም ፡ በኃያል
በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ አንድ
ሁነው ፡ ይጠፋሉ ፤
፷፰ ፤ ወይትነሣእ ፡ ጸድቅ ፡ እምንዋም ፤
ጻድቅ ፡ ማናቸውም ፣ ጻድቅ ፡
ሎጥ ፡ ከንዋመ ፡ ኃጢአት ፣ ከን
ዋመ ፡ ሐኬት ፡ ይነሣል ፤ አን
ድም ፡ ጌታ ፡ ከንዋመ ፡ ትዕግ
ሥት ፡ ይነሣል ፣
ወይትነሣእ ፡ ጥበብ ፡
ጥበብ ፡ ይገለጻል ፡
ወይትወሀብ ፡ ሎሙ ፣
ለሎጥ ፡ ለልጆቹ ፡ ይሰጣል ፣
ወእምኔሁ ፡ ይትገዘሙ ፡ አሥራወ ፡
ዓመፃ ፣
ኃጢአት ፡ የሚሠሩ ፡ ሰብአ ፡
ሰዶም ፣ ሰብአ ፡ ገሞራ ፣ ከሎጥ ፡
ተለይተው ፡ ይጠፋሉ ፤
፷፱ ፤ ወኃጥአን ፡ ይትኀጉሉ ፡ በሰ
ይፍ ፣
ሰብአ ፡ ከነዓን ፡ በሰይፈ ፡ ኢያሱ ፡
ይጠፋሉ ፣
ወእምነ ፡ ጽሩፋን ፡ ይትገዘሙ ፡
በኵሉ ፡ መካን ፤
እግዚአብሔርንም ፡ የሚሳደቡ ፡
ወገኖች ፡ ከየቦታው ፡ ሁሉ ፡
ይጠፋሉ ፣

፸ ፤ ወእለ ፡ ይሔልይዋ ፡ ለግፍዕ ፡
ወእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለጽርፈት ፡ ይት
ኀጉሉ ፡ በመጥባሕት ፣
ግፍን ፡ የሚያስቧት ፡ ስድብንም
የሚሳደቡ ፡ ሰብአ ፡ ከነዓን ፡ በመ
ጥባሕተ ፡ ኢያሱ ፡ ይጠፋሉ።

## ምዕራፍ ፷፫
## ጉባኤ

፩ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ትከውን ፡ ካል
ዕት ፡ ሰንበት ፡ ሳምኒት ፡ እንተ ፡
ጽድቅ ፣
እውነተኛ ፡ ምሥጢር ፡ የሚገ
ለጽባት ፡ ሁለተኛ ፡ የምትሆን ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስምንተኛ ፡ ሱባዔ ፡
ትሆናለች ፤ ካልዕት ፡ ለ፪ኛው ፤
ሳምኒት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ነው ፤
ውስጥ ፡ ለውስጥም ፡ ሱባዔ ፡
ሲቈጥር ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፤
ለዚያ ፡ ሳምንት ፣ ካልዕት ፡ እለ ፤
ሱባዔው ፡ የውሉድ ፡ ነውና ፤
ኢዮስያስ ፣ ኢዮአቄም ፡ ኢኮን
ያን ፣ ሰላትያል ፣ ዘሩባቤል ፣ አብ
ዩድ ፣ ኤልያቄም ፣ ናቸው ፣
ወይትወሀብ ፡ ላቲ ፡ ሰይፍ ፤
ለትሩፍ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣታል ፣
ከመ ፡ ይትገበር ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቅ ፡
እምእለ ፡ ይገፍዑ ፡ ወይትሜጠዉ ፡
ኃጥአን ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለጻድቃን ፣
በሚበድሉ ፡ በፋርስ ፡ በባቢሎን ፡
ሰዎች ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡

፲ ፡ ወይእዜኒ ፡ ስምዑኒ ፡ ደቂቅየ ፡
ወሑሩ ፡ በፍናዋተ ፡ ጽድቅ ፡
አሁንም ፡ ልጆቼ ፡ ስሙኝ ፡ በበጎ ፡
ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡

፲፩ ፡ ወኢትሑሩ ፡ በፍናዋተ ፡
ግፍዕ ፡
በግፍ ፡ ሥራዎች ፡ ጸንታችሁ ፡
አትኑሩ ፡ እላችኋለሁ ፡
እስመ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ለዓለም ፡
ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በፍኖተ ፡
ዓመፃ ፡
በግፍ ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡ የሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ይጠፋሉና ፡

፲፪ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ እምሄኖክ ፡ ጸሐፊ ፡
ዝ ፡ ኵሉ ፡ ትምህርተ ፡ ጥበብ ፡ እም
ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ስቡሕ ፡ ወመኰንነ ፡
ኵሉ ፡ ምድር ፡
የዓለም ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡
የምሆን ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ክቡር
ከምሆን ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡ የተ
ጻፈ ፡ አንድም ፡ የዓለም ፡ ሁሉ
መምህር ፡ ከሚሆን ፡ ከዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ ክቡር ፡ ከሚሆን ፡ ከጌታ
ተገልጻልኝ ፡ ከእኔ ፡ ከጸሐፊ ፡
ሄኖክ ፡ ተጻፈ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡
ከጸሐፊ ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡ የተገኘ ፡
አንድም ፡ ከጸሐፊ ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡
የተገኘ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የጥበብ ፡
ትምህርት ፡ ነው ፡

፲፫ ፡ ለኵሎሙ ፡ ውሉድየ ፡ እለ ፡
የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወለተ
ውልድ ፡ ደኃራውያን ፡ እለ ፡ ይገብሩ
ርትዐ ፡ ወሰላመ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለል
ጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ፍቅርንና ፡ የቀና ፡
ነገርን ፡ ለሚሠሩ ፡ ኋላም ፡ ለሚ
ወለዱ ፡ ለልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ትድ
ረስ ፡

፲፬ ፡ ኢትኅዝን ፡ መንፈስክሙ ፡ በእ
ዝማን ፡ እስመ ፡ መዋዕለ ፡ ወሀበ
ቅዱስ ፡ ወዓቢይ ፡ ለኵሉ ፡
ክቡር ፡ ገናና ፡ የሚሆን ፡ ንጹሕ
ጌታ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አዝማነ
ንስሓን ፡ ሰጥቷልና ፡ ኃጢአት ፡
ሠርታችሁ ፡ ገሃነም ፡ ወርዳችሁ ፡
በአዝማኑ ፡ መንግሥተ ፡ ለማየት ፡
ነፍሳችሁ ፡ እንዳታዝን ፡ ትሁን ፡

፲፭ ፡ ወይትነሣእ ፡ ጻድቅ ፡ እምን
ዋም ፡
ጻድቅ ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ከን
ዋመ ፡ ኃጢአት ፡ ይነሣል ፡
ይትነሣእ ፡ ወየኀልፍ ፡ በፍኖተ ፡
ጽድቅ ፡
በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖ
ራል ፡

ወእምቃለ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ አእመርኩ ፤

ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ሰምቼ ፡ ያወቅሁትን ፤

ወእምጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ ለበውኩ ፤

በጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ ልብ ፡ ያደረግሁትን ፡ እነግራችኋለሁ ፤

፹፩ ፤ ወአኀዘ ፡ እንከ ፡ ይትናገር ፡ ሄኖክ ፡ እመጻሕፍት ፤

ሄኖክም ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ይናገር ፡ ጀመር ፤

ወይቤ ፡ አነ ፡ ሳብዕ ፡ ተወለድኩ ፡

በቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ በመጀመሪያቱ ፡ ሱባዔ ፡ ሰባተኛ እኔ ፡ ተወለድኩ ፤ አንድም ፡ ሳብዐ ፡ ቢል ፡ ሰባተኛ ፡ ሆኜ ፡ ተወለድኩ ፤

አንድም ፡ በመጀመሪያው ፡ ሱባዔ ፡ አዳም ፤ ሴት ፤ ሄኖስ ፡ ቃይናን ፤ መላልኤል ፤ ያሬድ ፤ ሄኖክ ፤

፹፪ ፤ እስከ ፡ አመ ፡ ኮነኔ ፡ ወጽድቅ ፡ ተዐገሠ ፤

እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ እስኪፈረድ ድረስ ፡ ታገሠ ፤

ወትቀውም ፡ እምድኅሬየ ፡ በካልእት ፡ ሰንበት ፤

በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፤

ዓባይ ፡ እኪት ፤

ጽኑ ፡ ጥፋት ፡ ይሆናል ፤

፹፫ ፤ ወጕሕሉት ፡ በቈለት ፤

ተንኮል ፡ ትጸናለች ፤ ሄኖክ ፡ ብሎ ፡ ቆሚል ፤ ማቱሳላ ፤ ላሜህ ፤ ኖኅ ፤ ሴም ፡ አርፋክስድ ፤ ቃይናን ፡ ሳላ ፤

ወባቲ ፡ ትከውን ፡ ፍጻሜ ፡ ቀዳሚት ፤

በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ የመጀመሪያው ፡ መቅሠፍት ፡ ይሆናል ፤ የሰው ፡ መጨረሻ ፡ ይሆናል ፤ አናቦ ፡ የመጀመሪያው ፡ መቅሠፍት ፡ መጨረሻ ፡ ይሆናል ፤

፹፬ ፤ ወባቲ ፡ ይድኅን ፡ ብእሲ ፤

በሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ኖኅ ፡ ይድናል ፤

ወእምድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ ትልሕቅ ፡ ዓመፃ ፤

ሁለተኛው ፡ ሱባዔ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ኃጢአት ፡ ትበዛለች ፤

ወሥርዓተ ፡ ይገብር ፡ ለኃጥአን ፤

ለሰብእ ፡ ሰናዖር ፡ ዝርወተ ፡ ልሳን ፡ ያደርጋል ፤

፹፭ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ በሣልስት ፡ ሰንበት ፡ በተፍጻሜታ ፤

ከ፪ተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በኋላ ፡ በ፫ተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በመጨረሻው ፤

ይትኀረይ ፡ ብእሲ ፤

አብርሃም ፡ ይመረጣል ፤

ለተክለ ፡ ኮነኔ ፡ ጽድቅ ፤

እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ ለመሥራት ፤ አንድም ፡ ተክለ ፡ ኮነኔ ፡ ቢል ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ በመጠበቅ ፡

እስመ ፡ ብዙኃ ፡ ትሬእዩ ፡ በዲበ ፡
ምድር ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡
ታያላችሁና ፤

፲፪ ፤ እስመ ፡ ስነ ፡ ትወድዩ ፡
ላዕሌክሙ ፡ አንትሙ ፡ ዕደው ፡
ፈድፋደ እምአንስት ፤

እናንተ ፡ ወንዶች ፡ ከሴቶች ፡
ይልቅ ፡ ጌጥ ፡ ታጌጣላችሁ ፣
ስለሆነም ፡ ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
ታደርጋላችሁና ፤

ወኅብረ ፡ ፈድፋደ ፡ እምድንግል ፡

በመንግል ፤ በጌጥ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ከድንግሊቱ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡
መልክ ፡ ያለው ፡ በጌጥ ፡ ላይ ፡
ጌጥ ፡ ታጌጣለችሁና፤ አንድም ፡
በመንገለ ፡ አንስት ፡ ይላል ፣
በሴቶች ፡ ዘንድ ፡ አጊጣችሁ ፡
አምራችሁ ፡ ትታዩ ፡ ዘንድ ፡
ታጌጣላችሁና፤

፲፫ ፤ በመንግሥት ፤

በመንግሥት ፡ ያላችሁ ፡ ይመስ
ላችኋልና ፤

ወበዕበይ ፡ ወበሥልጣን ፤

በገናንነት ፡ በሥልጣን ፡ ያላችሁ
ይመስላችኋልና፤

ወበብሩር ፡ ወወርቅ ፡ ወሜላት ፡
ወክብር ፤

በወርቅና ፡ በብር ፡ በነጭ ፡
ሐርም ፡ የከበርን ፡ ይመስላች
ኋልና ፤

፲፬ ፤ ወመባልዕት ፡ ከመ ፡ ማይ
ይትከዓዉ ፣

መብሎችም ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ በዝ
ተው ፡ በፊታችሁ ፡ ይቀርባሉ ፤

ወበእንተዝ ፡ ትምህርት ፡ ወጥበብ ፡
አልቦሙ ፤

ስለዚህም ፡ በዝተው ፡ ስለቀረቡ ፡
ትምህርት ፣ ጥበብ ፣ የላቸውም፤

፲፭ ፤ ወቦቱ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ኅቡረ ፡
ምስለ ፡ ንዋያቲሆሙ ፡ ወምስለ ፡
ኵሉ ፡ ስብሐቶሙ ፡ ወክብሮሙ ፤

መባልዕት ፡ በዝተው ፡ ስለቀረቡ ፣
ጥበብ ፣ ትምህርት ፡ ስለሌላቸው፡
ከገንዘባቸው ፡ ከክብራቸውና ፡
ከጌትነታቸው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
አንድ ፡ ሁነው ፡ ይጠፋሉ ፤

፲፮ ፤ ወበጽእለት ፡ ወበንዴት፤

በጽዕለተ ፡ ነፍስ ፡ (በስድብ) ፡
በንዴተ ፡ ነፍስ ፡ ሲሆኑ ፤

ወበቀትለ ፡ ነፍስ ፤

በቀትለ ፡ ነፍስ ፡ ወበቀል ፡ ቢል ፣
በጽኑ ፡ በቀልም ፡ ሆነው ፡ ሲኖሩ፤

ወበንዴት ፡ ዓቢይ ፤

በፍጹም ፡ ንዴተ ፡ ነፍስ ፡
ሲኖሩ፣

ትትወደይ ፡ መንፈሰሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፤
ነፍሳቸው ፡ በገሃነም ፡ ትወድቃለች ፤
፲፯ ፤ መሐልኩ ፡ለክሙ ፡ ኃጥአን ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤
ተራራ ፡ በባሕርዩ ፡ ተገኘ ፡ እንዳልነበረ ፤ ወኢይከውን ፤ እንግዲህም ፡ መገዛት ፡ እንደሌለበት ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፤
ወኢወግር ፡ ለብእሲት አመተ ፤
ኮረብታም፡ ለሴት ፡ ተገኘ ፡ እንዳይደለች ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፤
፲፰ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአትኒ ፡ ኢተፈነወት ፡ዲበ ፡ ምድር ፤
ተራራ ፡ ኮረብታ ፡ በባሕርያቸው ፡ መገዛት ፡ እንደሌለባቸው፡ ኃጢአትም ፡ የባሕርይ ፡ ሁና ፡ አልተፈጠረችም ፤
አላ ፡ሰብእ ፡ እምርእሰሙ ፡ ፈጠርዋ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ከልቦናቸው፡ አንቅተው ፡ ሠሯት ፡ እንጂ ፤
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፡ እለ ገብርዋ ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ለፍጹም ፡ ጥፋት ፡ ይሆናሉ ፤ አንድም ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤ ዓበይት ፡ ነቢያት ፡ አሪትን ፤ ነዋሪት ፤
ቀዋሚት፡ ሕግ ፡ ናት ፡ብለው ፡ እንዳላስተማሩ ፤
ወኢወግር ፤ ለብእሲት ፡ አመተ፤
ደቂቅ ፡ ነቢያትም ፡ አምሳል ፡ መርገፍ፡ የምትሆን ፡ አሪትን ፡ ነዋሪት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ እንዳላስተማሩ ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአት ፡ ኢተፈነወት ፡ አሁን ፡ እንደተናገርሁት ፡ ኃጢአትም ፡ ነዋሪት ሕግ ፡ ሁና ፡ አልተሠራችም ፤
አላ ፡ ሰብእ ፡ እምርእሰሙ ፡ ፈጠርዋ ፤ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ልብ ወለድ ፡ አንቅተው ፡ ቀዋሚት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ አስተማሯት ፡ እንጂ ፡
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፤
ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ለጽኑ ፡ መርገም ፡ ይሆናሉ፤ (ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ይባላሉ ፤)
፲፱ ፤ ወምክነት ፡ ለብእሲት ፡ ኢተውህባ ፤
ለሴት፡ ምክነት፡ አልተሰጣትም፤
አላ ፡ በግብረ ፡ እዴሃ ፡ ትመውት ፡ ዘእንበለ ፡ ውሉድ ፤

በእጇ ፡ ይዛ ፤ በቃሏ ፡ ተናግራ ፤
በሠራቸው ፡ ኃጢአት ፡ ያለልጅ
ትሞታለች ፡ እንጂ ፤ ኢሳይያስ ፡
አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ዘእፈጥር ፡
መካነ ፡ ወአወልድ ፡አለ ፤ከዚህ ፡
እንዲህ ፡ አለ ፤ አይጣላም? ቢሉ ፡
አይጣላም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሄኖክ ፡
ነው ፤ ምክንት ፡ በደዌ ፡ በኃጢ
አት ፡ ነው ፤ አነ ፡ ዘእፈጥር ፡
መካነ ፡ አለሳ ፡ ቢሉ ፡ እስክት
ወልድ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፤ አነ ፡
ዘእፈጥር ፡ መካነ ፡ አለ ፤ አንድም ፡
አዝኖ ፡ ተክዞ ፡ የወለዱት ፡ ልጅ ፡
ይጠቅማልና ፡ እስኪወልዱ ፡
ድረስ ፡ ያለውን ፡ ዘእፈጥር ፡
መካነ ፡ አለ ፤ አንድም ፡ መጻእ
ያትን ፡ አለማወቅ ፡ ለነፍስ ፡
አልተሰጣትም ፤ አላ ፡ በእንተ ፡
ግብረ ፡ እደዊሃ ፤ በኃጢአቷ ፡
ምክንያት ፡ መጻእያትን ፡ ሳትና
ገር ፡ ትሞታለች ፡ እንጂ ፤
፮ ፤ መሐልኩ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥአን ፡
በቅዱስ ፡ ወዓቢይ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡
ግብርክሙ ፡ እኩይ ፡ ክሡት ፡ ውእቱ ፡
በሰማያት ፤
ኃጥአን ፡ ክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ ሁሉ ፡
በሰማይ ፡ የተገለጸ ፡ እንደሆነ ፤

ወአልብክሙ ፡ ግብረ ፡ ግፍዕ ፡ ክዱን ፡
ወኢኅቡዕ ፤
የተሠወረ ፡ የግፍ ፡ ሥራም ፡
እንደሌላችሁ ፡ በገናና ፡ በክበረ
ስሙ ፡ ምዬ ፡ ነገርኋችሁ ፤
፯ ፤ ወኢታምስሉ ፡ በመንፈስክሙ ፤
በልቡናችሁ ፡ የሚሰወር አታስ
መስሉት ፤
ወኢትበሉ ፡ በልብክሙ ፡
በልቡናችሁ ፡ ይሰወርልናል ፡
አትበሉ ፤
እስመ ፡ ኢተአምሩ ፡ ወኢትሬእዩ ፡
ኵሉ ፡ ኃጢአተክሙ ፡ ዘበሰማይ ፡
ይጸሐፍ ፡ ሀሎ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡
በቅድሜሁ ፡ ለልዑል ፤
በሰማይ ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ ይጻፍ
ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ አታዩም ፤
አታውቁምና ፤
፰ ፤ ወእምይእዜ ፡ ተአምሩ ፡
እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግፍዕክሙ ፡ ዘት
ገፍዑ ፡ ይጸሐፍ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡
እስከ ፡ ዕለተ ፡ ኵነኔክሙ ፤
ፍርድ ፡ እስከሚፈረድባት ፡
እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ
የበደላችሁት ፡ በደል ፡ በየቀኑ
ሁሉ ፡ እንዲጻፍባችሁ ፡ ታውቃ
ላችሁ ፤
፱ ፤ አሌ ፡ ለክሙ ፡ አብዳን ፡
እስመ ፡ ትትኃጐሉ ፡ በዕበድክሙ ፤

የማይገታ ፡ የማይፈጸም ፡ ደም ለሚፈስስበት ፡ ቀን ፡ ኃጢአት ፡ ተዘጋጅቷልና ፡ ለእናንተ ፡ ለኃ ጥአን ፡ ጻግመኛ ፡ እምልላችኋ ለሁ ፤ እነግራችኋለሁ ፤

፰ ፤ ወይሰግዱ ፡ ለዕብን ፤
ወለእለ ፡ ይሰግዱ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለደንጊያ ፡ ለሚሰግዱ ፡ ሰዎች ፤
ወእለ ፡ ይገልፉ ፤
ወለእለ ፡ ይገልፉ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለጣዖት ፡ ለሚሰግዱ ፤ ጣዖት ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፤
ምስለ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፤
የወርቅ ፡ የብር ፡ ምስል ፡ ለሚሠሩ ፤
ወዘዕፅ ፡ ወዘልሕኵት ፤
ከእንጨትና ፡ ከሸክላ ፡ ተቀርጾ ለሚሠራ ፡ ምስል ፤
፱ ፤ ወእለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለነፍሳት ፡ ርኵሳን ፤
ለረከሱ ፡ ለረቂቃኑ ፡ለግዙፋኑ ፤
ወለአኩያን ፡ አጋንንት ፤
ለክፉዎችም ፡ አጋንንት ፡ ለረቂ ቃኑ ፤ አንድም ፡ ለነፍሳት ፡ ለር ኵሳን ፡ ሰዎች ፤ ወለአጋንንት ፡ በቁሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ለሚሰግዱ ሰዎች ፤
ወለኵሉ ፡ ጣዖት ፡ ወለምሕራማት ፤
ለጣዖቱም ፡ ለመስገጃው ፡ ሁሉ ፡ ይሰግዳሉ ፤

፲ ፤ ወኵሉ ፡ ረድኤት ፡ ኢይትረከብ ፡ እምኔሆሙ ፤
እምኔሆሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ነው ፤ ከእነርሳቸውም ፡ ከጣዖታት ፡ ረድኤት ፡ ሁሉ ፡ አይገኝም ፤
ወይትረስዑ፡ በእንተ ፡ ዕበደ ፡ ልቦሙ፤
ከልቦናቸውም ፡ ድንቁርና፡ የተነሣ ፡ ከሥላሴ ፡ ልቡና ፡ ይዘነጋሉ ፤
ወይጼለላ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ በፍርሀተ ልቦሙ ፤
በልቦናቸው ፡ ፍርሀት ፡ የልቡና ቸው ፡ ዓይኖች ፡ በድንቁርና ፡ ይያዛሉ ፤
፲፩ ፤ ወበርእየ ፡ አሕላሞሙ ፡ በሙ ይረስዑ ፤
የሐሰት ፡ ሕልም ፡ አለምን ፤ አለ ምን ፡ በማለታቸው ፡ ሕግ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ ይዘነጋሉ ፤
ወይፈርሁ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብሮሙ ፡ በሐሰት ፡ ገብሩ ፤
ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ በሐሰት ፡ ሠርተዋልና ፡ ይፈራሉ ፤
ወሰገዱ ፡ ለዕብን ፡ ወይትኀጉሉ ፡ በምዕር ፤
ለደንጊያውም ፡ ሰግደዋልና ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉ ፤

ወኢይሔልዩ ፡ ዲበ ፡ ኃጢአትክሙ ፤
በኃጢአታችሁ ፡ ምክንያት ፡ ይወርዱ ፡ ዘንድ ፡ አያስቡምና ፤
፻፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ ሀቡ ፡ አምኃ ለዝናም ፡ ከመ ፡ ኢይትከላአ ፡ ወሪደ ዲቤክሙ ፤
አሁንም ፡ ዝናም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መውረዱን ፡ እንዳይከለከል ፤
ወጠል ፤
ጠልም ፡ ከእናንተ ፡ መውረድን እንዳይከለከል ፤
እመ ፡ ተመጠወ ፡ እምኔክሙ ፡ ወርቀ ፣ ወብሩረ ፣ ከመ ፡ ይረድ ፤
ከእናንተ ፡ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ ተቀብሎ ፡ ይወርድ ፡ እንደሆነ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ስጡ ፤
፻፺ ፤ ወሶበ ፡ ይወድቅ ፡ እምኔክሙ ፡ አስሐትያ ፣ ወሐመዳ ፣ ወቊረ ፡ ዚአሆሙ ፤
ውርጭ ፣ ዋግ ፡ በእናንተ ፡ ቢወድቁባችሁ ፡ የእነርሱም ፡ ቅዝቃዜ ፡ ቢደረግባችሁ ፤
ወኵሉ ነፋሳተ ፡ ሐመዳ ፤
ዋግን ፡ የሚያመጡ ፡ ነፋሳትም ፡ ሁሉ ፤
ወኵሉ ፡ ፃዕራተ ፡ ዚአሆሙ ፡
እሊህ ፡ የሚያመጡት ፡ ጭንቀትም ፡ ቢያገኛችሁ ፣
በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ኢትክሉ ፡ ቀዊመ ፡ ቅድሜሆሙ ፤
በእነዚያ ፡ ወራት ፡ በእነርሱ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይቻላችሁም ።

## ምዕራፍ ፻፱

## ጉባኤ ፤

፩ ፤ ጠይቅዋ ፡ ለሰማይ ፡ ኵልክሙ ውሉደ ፡ ሰማይ ፤ ወኵሎ ፡ ግብሮ ፡ ለልዑል ፤
በሰማያዊ ፡ ግብር ፡ የምትኖሩ ፣ ሰማያዊ፡ ሕግን ፡ የምትጠብቁ ፣ ሰማይን ፡ መርምሯት ፣ ተረዷት፤ አንድም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ የምትኖሩ ፡ ተረዷት ፤ አንድም ፡ ውሉድ ፡ ሰማያውያን ፡ ይላል ፤ ሰማያውያን ፡ ውሉድ ፡ ሰማያዊ፡እግዚአብሔርን፡ አስቡ ፤ ደግ ፡ መጽሐፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በጀመረበት ፡ ይጨርሳል ፣
ወፍርሁ ፡ እምኔሁ ፤ ወኢትግበሩ ፡ እኩየ ፡ በቅድሜሁ ፤
በፊቱ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳትሠሩ ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ ፍሩ ፤
፪ ፤ እመ ፡ ዐጸወ ፡ መስኮተ ፡ ሰማይ፡ ወከልአ ፡ ዝናመ ፣ ወጠለ ፣ ከመ ፡ ኢይረድ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በእንቲአክሙ ፤
ሰማይ ፡ መስኮቱን ፡ ቢዘጋ ፤ አንድም ፡ መስኮተ ፡ ሰማይ ፡ ቢል ፡ ጌታ ፡ የሰማይን ፡ መስኮት ፡

ቢዘጋ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፣ ጠል፡
ለመከር ፣ ከመስጠት ፡ ቢከለክል ፣
ሚ ፡ ሀለወክሙ ፡ ትግበሩ ፤
ምን ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አላችሁ ?
፫ ፤ ወእመ ፡ ፈነወ ፡ መዓቶ ፡ ዲቤ
ክሙ ፤
መዓቱን ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ቢያ
መጣባችሁ ፤
ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ ምግባሪክሙ ፤
በሥራችሁ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ መዓ
ቱን ፡ ቢያመጣ ፡ ምን ፡ ታደ
ርጉ ፡ ዘንድ ፡ አላችሁ?
አኮኑ ፡ አንትሙ ፡ እለ ፡ ታስተ
በቍዕዎ፤
እርሱን ፡ የምትለምኑት ፡ አይደ
ለምን ፤
፬ ፤ እስመ ፡ ትትናገሩ ፡ ዲበ ፡
ጽድቀ ፡ ዚአሁ ፡ ዓቢያተ ፡ ወጽ
ኑዓተ፤
በጌትነቱ ፡ ላይ ፡ ታላላቅ ፡ ነገርን
ጽኑ ፡ ጽኑ ፣ ነገርን ፡ ትናገራ
ላችሁና ፤ አንድም ፡ አኮ ፡
አንትሙ ፡ እለ ፡ ታስተበቍዕዎ ፡
ቢል ፣
ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ ነገር ፡ ትናገራላ
ችሁና ፡ የምትማልዱት ፡ አይደ
ለም፤
ወአልብክሙ ፡ ሰላም፤
ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የላችሁም ፤

፭ ፤ ኢትሬእይዎሙኑ ፡ ለነገሥተ ፡
አሕማር ፡ እፎ ፡ ይትሀወኩ ፡ እሞገድ፤
ከማዕበሉ ፡ ከሞገዱ ፡ የተነሣ ፡
ነጋድያን ፡ እንዴት ፡ እንዲታ
ወኩ ፡ አታዩዋቸውምን ፤
ወያንቀለቅሉ ፡ እምነፋሳት ፡ አሕማ
ሮሙ ፡ ወይትመነደቡ ፤
ከማዕበሉ ፡ ከሞገዱ ፡ የተነሣ ፡
እንዲታወኩ ፡ እንዲጨነቁ ፡
በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ የሚ
ሄዱ ፡ ነጋድያንን ፡ አታዩዋቸ
ውምን ፤
፮ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይፈርሁ ፣
መርከቡ ፡ ስለተነዋወጠባቸው ፡
ይፈራሉ ፤ አንድም ፡ ለሚያመ
ጣው ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አለ ፣
እስመ ፡ ኵሉ ፡ ንዋዮሙ ሠናይ ፡
ይወፅእ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ምስሌ
ሆሙ ፤
መልካሙ ፡ ያማረ ፡ ያማረው ፡
ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ከቤት ፡ ወደባሕር ፡
ይወጣልና ፤ አንድም ፡ ከእርሳ
ቸው ጋር ፡ የሚሠጥም ፡ ይመስ
ላቸዋልና ፡ ስለዚህም ፡ ይፈራሉ፤
፯ ፤ወሠናየ ፡ ኢይሔልዩ ፡ በልቦሙ ፣
እንሞታለን ፡ እንጂ ፡ እንድና
ለን ፣ እንሰጥማለን ፡ እንጂ እንወ
ጣለን ፡ ብለው ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡
አያስቡምና ፣በእንተ ፡ ዝንቱ ፡
ብለህ ፡ እሠር ፤

፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ይወዲ ፡ ቃሉ ፡ ዲቤ
ከሙ ፤
የመዓቱን ፡ ቃል ፡ ወደእናንተ ፡
ባመጣው ፡ ጊዜ ፤
እኩ ፡ ትትማህከው ፡ ወትፈርሁ ፣ ትደ
ነግፁ ፣
ትወድቁ ፡ ሲል ፡ ነው ፣ የምት
ፈሩ ፡ የምትደነግጡ ፣ የምትወ
ድቁ ፣ አይደለምን ?
ወኵሎሙ ፡ ብርሃናት ፡ ይትማህ
ከዉ ፡ ወይትሀወኩ ፡ በፍርሀት ፡
ዓቢይ ፤
ብርሃኖችስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡
ፍርሀት ፡ ተይዘው ፡ የሚፈሩ ፣
የሚደነግጡ ፡ አይደለምን ፤
፲፬ ፤ ወኵላ ፡ ምድር ፡ ትትማህከው ፡
በፍርሀት ፡ ዓቢይ ፤
ትፈርህ ፣ ትደነግፅ ፣ ሲል ፡
ነው ፤ ምድርስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ
ፍርሀት ፡ ተይዛ ፡ የምትን
ቀጠቀጥ ፡ አይደለምን፣
ወትርዕድ ፤
ለኀልፈት ፡ ትቀርባለች ፣
ወትጓጕዕ ፣
ለኀልፈት ፡ ትቸኩላለች ፤
፲፭ ፤ ወኵሎሙ ፡ መላእክት ፡ ይፌ
ጽሙ ፡ ትእዛዞሙ ፤
መላእክትም ፡ ሁሉ ፡ የታዘዙ
ትን ፡ ይፈጽማሉ ፤
ወይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይትኀብኡ ፡
እምቅድመ ፡ ዓቢየ ፡ ስብሐት፤
ከክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ ፊት
ሊሰወሩ ፡ ይወዳሉ ፤
፲፮ ፤ ወይርዕዱ ፡ ደቂቀ ፡ ምድር ፡
ወይትሀወኩ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡
ይርዳሉ ፡ (ይንቀጠቀጣሉ) ፡ ይታ
ወካሉ ፤
ወአንትሙ ፡ ኃጥአን ፡ ርጉማን ፡ ለዓ
ለም ፤
እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ ለዘለዓ
ለሙ ፡ የተረገማችሁ ፡ ናችሁ ፣
ወአልብክሙ ፡ ሰላም ፤
ፍቅር ፡ አንድነትም፡ የላችሁም፤
፲፯ ፤ ኢትፍርሁ ፡ አንትሙ ፡ ነፍ
ሳተ ፡ ጻድቃን ፤
እናንተ ፡ የጻድቃን ፡ ሰውነቶች
አትፍሩ ፤
ወተሰፈዉ ፡ እለ ፡ ሞትክሙ ፡ በጽ
ድቅ ፤
በእውነት ፡ ነገርም ፡ የሞታችሁ
ሰዎች ፡ ዋጋችሁን ፡ እንድታገኙ
ተስፋ ፡ አድርጉ ፤
፲፰ ፤ ወኢትኅዘኑ ፡ እስመ ፡ ወረደት ፡
ነፍስክሙ ፡ ውስተ ፡ ዓቢይ፡ ምን
ዳቤ፤
ሰውነታችሁ ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡
ላለች ፤

ወራት ፡ ለእናንተ ፡ ድካምን ፡
ደከምን፡ አትበሏቸው ፤ አንድም ፡
ዕጣን ፡ በምንወግርበት ፣ ዝክር፡
በምንዘክርበት ፡ ወራት ፡ ደከምን ፡
አትበሏቸው ፤
፲፫ ፤ ወኮሎ ፡ ሥራሐ ፡ ርኢነ፤
መከራውን ፡ ሁሉ ፡ አየን ፣
ወእኩያተ ፡ ብዙኃተ ፡ረከብነ ፤
ብዙ ፡ መከራዎችንም ፡ ተቀበ
ልን ፣
ወተወዳእነ ፡ ወውኅድነ ፣
ጨርሰን ፡ ጠፋን ፤
ወንእሰት ፡ መንፈስነ ፡ ወተኀጕልነ ፣
ሰውነታችን ፡ እንስንስ ፡ አለች ፣
በዚህም፡ ጠፋን ፡ አትበሏቸው ፤
፲፬ ፤ ወአልቦ ፡ ዘረድአነ ፤
በነገር ፡ በጸሎት ፡ የረዳን ፡
የለም ፡ አትበሏቸው ፤
ወበምግባር ፡ ስእነ ፣
በምናቀርበው ፡ ዕጣን ፣
በምንዘክረው ፡ ዝክር ፡ መዳን
ተሳነን ፡ አትበሏቸው ፤
ወኢምንተኒ ፡ ኢረከብነ ፤
በእነርሱም ፡ ሥራ ፡ ስንደክም ፡
ምንም ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ አላገኘ
ንም ፤
ወተጽዕርነ ፡ ወተኀጕልነ ፣
በመከራውም ፡ ተጨነቅን ፡ ጠፋን፡
አትበሏቸው ፤
፲፭ ፤ ወኢተሰፈውነ ፡ ከመ ፡ ንርአይ ፡
ሕይወተ ፡ ዕለተ ፡ እምዕለት ፤
ከዛሬ ፡ ነገ ፣ ከነገ ፡ ሣልስት ፣
ሕይወትን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡
ተስፋ ፡ አላደረግንም ፡ አት
በሏቸው ፤
ወተሰፈውነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ርእሰ ፤
ገዥ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡
አደረግን ፤
ወኮነ ፡ ዘነበ ፣
ተገዥ ፡ ሆነ ፤
ዓመውነ ፡ እንዘ ፡ ንትጌበር ፣
ሥራውን ፡ ስንሠራ ፡ ደከምን ፤
፲፮ ፤ ወኢሠለጥነ፡ ዲበ ፡ ዓማፅነ፣
በገንዘባችን ፡ አልሠለጠንም ፤
ወኮነ ፡ መባልዕተ ፡ ለኃጥአን ፣
ለኃጥአንም ፡ መብሎችን ፡ ሆንነ ፣
ለነገሥታቱ፡ ለመኳንንቱ ፡ምግብ
ሆንን ፤
ወዓማፅያን ፡ አክበዱ ፡ ላዕሌነ ፡ አር
ዑተ ፡ ዚአሆሙ ፤
በደለኞች ፡ ሰዎችም ፡ በእኛ ፡
ላይ ፡ አገዛዛቸውን ፡ አጸኑብን ፤
፲፯ ፤ ወተሠልጡ ፡ ዲቤነ ፡ እለ ፡
ይጸልኡነ ፤ ወእለ ፡ ይደጕፁነ ፤
እኛን ፡ የሚጠሉን ፣ የሚወጉን ፡
ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ሠለጠኑብን ፤

ወለእለ ፡ ይጸልኡነ ፡ አትሐትነ ፡
ክሣደነ ፤
ለሚጠሉንም ፡ ለጠላቶቻችን ፡
አንገታችንን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደ
ረግን ፤
ወኢመሐሩነ ፤
እነርሱ ፡ ግን ፡ አልራሩልንም ፡
አትበሏቸው ፤
፲፰ ፤ ወፈቀድነ ፡ ንሖር ፡ እምኔሆሙ ፡
ከመ ፡ ንንፍጽ ፡ ወናዕርፍ ፤
ከእነርሱ ፡ ሸሽተን ፡ ከመከራው፡
ልናርፍ ፡ ወደድን፤
ወኢረከብነ ፡ ኀበ ፡ ንጕየይ ፡ ወንድ
ኅን ፡ እምኔሆሙ ፤
ከነሱም ፡ ሸሽተን ፡ የምንድንበት
ቦታ ፡ አላገኘንም፤
፲፱ ፤ ወሰከይናሆሙ ፡ ኀበ ፡ መላእ
ክት ፡ በምንዳቤነ ፤
በመከራችን ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻ
ችነን ፡ ከአለቆች ፡ ከሰስናቸው ፤
አንድም ፡ ከመላእክት ፡ ዘንድ ፡
ከሰስናቸው ፡
ወጸራሕነ ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ይበልዑነ ፤
ገንዘባችነን ፡ በሚበሉብን ፡ በጠ
ላቶቻችን ፡ ወደ ፡ አለቆች ፡
ጮኽን ፤ አንድም ፡ ወደ ፡
መላእክት ፡ ጮኽን ፤ አንድም፡
ወሰከይናሆሙ ፡ ልመናችንን ፡
አድርሱልን ፡ ብለን ፡ ጻድቃንን፡
ወደ መላእክት ፡ አካሰስናቸው፤
ወጸራሕነ ፤ በሚበድሉን ፡ በጠላ
ቶቻችን ፡ ጩኸታችንን ፡ ወደ ፡
መላእክት ፡ አድርሱልን ፡ ብለን፡
ለጻድቃን ፡ ጮኽነ ፤
ወጽራሐ ፡ ዚአነ ፡ ኢይርእዩ ወኢይ
ፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ቃለነ ፤
ኢይሬእዩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ልመና
ችንን ፡ ጻድቃን ፡ መላእክት ፡
አይሰሙም ፤
፳ ፤ ወይረድዕዎሙ ፡ ለእለ ፡ የሀይ
ዱነ ፡ ወይበልዑነ ፤
ለሚቀሙን ፡ ገንዘባችንንም ፡
የሚበሉብንን ፤
ወለእለ ፡ አውኀዱነ ፤
ያሳነሱንን ፤
ወየኀብኡ ፡ ግፍዖሙ ፤
ግፋቸውንም ፡ ይሰውሩላቸዋል
እንጂ ፤
ወኢያወጽኡ ፡ እምኔነ ፡ አርዑቶሙ ፤
አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፉል
ንም ፤
እለ ፡ ይበልዑነ ፤
ገንዘባችንን፡የሚበሉብንን፡ሰዎች፡
አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፉል
ንም ፤

፲፮ ፤ ወየሐውሩ ፡ እሙንቱሂ ፡ በኀበ ተጽሕፈ ፡ ሎሙ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፤

እነርሱም ፡ በተጻፈላቸው ፡ ዘመኖችና ፡ ቀኖች ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ አንድም ፡ በኀበ ፡ ኢተጽሕፈ ፡ ሎሙ ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ቀን ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ኑራችሁ ፡ ትመጣላችሁ ፤ ተብሎ ፡ ወዳልተጻፈላቸው ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ገነት ፤ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፤ ጻድቃን ፡ ይሔዳሉ ::

ተፈጸመ ፡ ራእየ ፡ ሄኖክ ፡ ነቢይ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፤

ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ነቢዩ ፡ ሄኖክ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ተፈጸመ ::

ጉባዔ ፡ ሄኖክ ፡ ፴ ፡ ወ፩ዱ ፡ ዘኊለቈ ፤

ሄኖክ ፡ የቆጠረው ፡ ሠላሳ ፡ አንዱ ፡ ጉባኤ ፤

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ስነሣሥት ፡ ለአስጀመረን ፤ ስተጋግት ፡ ለአስፈጸመን ፡

ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፤

<u>አሜን ::</u>